




# የአካባቢ ሳይንስ



## የተማሪ መጽሐፍ

## 2ኛ ክፍል

የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል መንግሥት ትምህርት ቢሮ





# የአካባቢ ሳይንስ

## የተማሪ መጽሐፍ

## 2ኛ ክፍል


### አዘጋጆች፡-

1. ፀዳለ ኃ/የሱስ
2. ተስፋዬ ዓለማየሁ
3. አስረስ አዛዥ

### አርታኢ፡-

1. ገዝሙ ስዩም

### ጥራት አረጋጋጮች

1. ዘላለም ለገሰ
2. ዝናው ዱባለ
3. መሃመድናጂ እስማኤል

### ሰዓሊ፡-

1. ሃይማኖት ኬሜቶ

### ሌያውት ዲዛይን፡-

1. ኃይለማርያም መለሰ (MSc.)



የደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/መንግሥት ትምህርት ቢሮ

# © የቅጂ መብት

ይህ መጽሐፍ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ ተዘጋጅቶ በደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦች ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት በኩል በተገኘ የገንዘብና የቴክኒክ ድጋፍ ተዘጋጅቶ አጠቃላይ የሕትመት ወጪው በደቡብ ብሔሮችና ብሔረሰቦች ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት ተሸፍኗል።

የመጽሃፉ ሕጋዊ ቅጂ ባለቤት © 2015 ዓ.ም የደቡብ ብሔሮችና ብሔረሰቦች ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት ትምህርት ቢሮ ነው።

# ማውጫ


መግቢያ ........................................................i

## ምዕራፍ አንድ ...............................1

## የወረዳችን መገኛ.................................. 1

1.1. የመገኛ ትርጉም ........................................................ 2
1.2. የአንጻራዊ መገኛ ትርጉም ............................................. 3
1.3. የወረዳችን አንጻራዊ መገኛ............................................. 4
1.4. የአጎራባች ወረዳዎች ስም እና መገኛቸዉ ............................... 6

## ምዕራፍ ሁለት.............................10

## ሳይንስን ማስተዋወቅ................................ 10

2.1. ዉጫዊ የሰዉነት ክፍሎቻችንና የስሜት ሕዋሳት ......... 11
2.1.1. ዉጫዊ የሰዉነት ክፍሎቻችን ........................................ 11
2.1.2. የስሜት ሕዋሳት እና ጥቅሞቻቸዉ .................................... 13
2.2. የቁሶች አካላዊ ባሕሪያት ................................................ 21
2.3. የብርሃን ምንጮች .......................................................... 23

## ምዕራፍ ሦስት........................28

### የተፈጥሮ አካባቢያችን ........................ 28

3.1. የአየር ሁኔታ እና የአየር ንብረት ........ 29

3.2. በወረዳችን ዉስጥ የሚገኙ እፅዋት ........ 32

3.2.1. እፅዋት........ 32

3.2.2. ዋና ዋና የእፅዋት ክፍሎች እና ተግባሮቻቸዉ........ 33

3.2.3. ለእፅዋት እድገት አስፈላጊ የሆኑ ነገሮች........ 38

3.2.4. ኮምፖስት ........ 40

3.3. በወረዳችን ዉስጥ የሚገኙ እንስሳት........ 43

3.3.1. እንስሳት ........ 43

3.3.2. የእንስሳት ጥቅም ........ 44

3.3.3. የእንስሳት ምደባ........ 46

3.4. በወረዳችን ዉስጥ የሚገኙ የተፈጥሮ ሐብቶች........ 59

3.4.1. የተፈጥሮ ሀብት ........ 59

3.4.2. የተፈጥሮ ሀብት ዓይነቶች........ 60

3.5. አካባቢያችንን መንከባከብ ........ 64

3.5.1. በአካባቢያችን የሚገኙ የተፈጥሮ ሀብት እንክብካቤ........ 64

3.5.2. በአካባቢያችን የሚገኙ ሰዉ ሰራሽ ሀብት እንክብካቤ........ 68

## ምዕራፍ አራት........................75

### ማህበራዊ አካባቢያችን........................ 75

4.1. የቤተሰብ አባላት እና ፍላጎቶቻቸው ........ 76

4.1.1. የቤተሰብ አባላት መሠረታዊ ፍላጎት ........ 76

4.1.2. የቤተሰብ የጤና አጠባበቅ ፋይዳዎች (ጥቅሞች) ........ 78

4.1.3. የትምህርት ቤት ማህበረሰብ እና የአካባቢ ማህበረሰብ ፍላጎት 81
4.2. በትምህርት ቤት የተማሪዎች አቻ ግንኙነት እና ተግባራት ....... 82
4.2.1. በትምህርት ቤት የተማሪዎች አቻ ግንኙነት ......................... 83
4.2.2. በትምህርት ቤት የተማሪዎች ተግባራት ............................... 84
4.2.3. የትምህርት ቤት ደንብ እና ስነ-ስርዓት ......................... 84
4.3. የግል እና የአካባቢ ንጽህና አጠባበቅ ................................ 86
4.3.1. የግል ንጽህና አጠባበቅ .................................................. 86
4.3.2. የአካባቢ ንጽህና አጠባበቅ ............................................... 87
4.3.3. የትምህርት ቤት ንጽህና አጠባበቅ.................................. 89

## ምዕራፍ አምስት ......................94

### የተለየ ትኩረት የሚፈልጉ ቁልፍ ጉዳዮች ..... 94

5.1. የመንገድ ትራፊክ ደህንነት .................................................. 95
5.1.1. የመንገድ ትራፊክ ደህንነት................................................ 95
5.1.2. የመንገድ ትራፊክ ደህንነት ሕጎች ....................................... 96
5.2. ጥሩ የጤና አጠባበቅ ልማድ ................................................. 98

# መግቢያ

ይህ የሁለተኛ ክፍል አካባቢ ሳይንስ ትምህርት የተማሪዎች መማሪያ መጽሐፍ በአዲሱ ስርዓተ ትምህርት ላይ ተመስርቶ የተዘጋጀ ነው፡፡ መጽሐፉ የአካባቢን ነባራዊ ሁኔታዎችን መሠረት በማድረግ የተዘጋጀ ሲሆን በውስጡ አምስት ምዕራፎችን ያካተተ ነዉ፡፡ እነዚህም የወረዳችንመገኛ፣ ሳይንስን ማስተዋወቅ ፣ የተፈጥሮ አካባቢያችን ፣ ማህበራዊ አካባቢያችን እና ልዩ ትኩረት የሚሹ ቁልፍ ጉዳዮች ናቸዉ፡፡በመሆኑምመምህራን የዉድ ተማሪዎቻቸዉን አካላዊ እናሥነ አዕምሮዊ ዕድገት ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ከትምህርቱ የሚጠበቅባቸዉን እዉቀት፣ አመለካከት እና ክህሎት ለማምጣት ጥረት ማድረግ የሚጠበቅባቸዉ ሲሆን ተማሪዎች ደግሞ በመምህራኖቻቸዉ አማካኝነት በየክፍለ ጊዜዉየሚቀርብላቸዉን ትምህርት በሚገባ መከታተልና ከፍተኛ ተሳትፎ በማድረግ መማር ይኖርባቸዋል፡፡

# ምዕራፍ አንድ

# የወረዳችን መገኛ

## ከምዕራፉ የሚጠበቁ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች

ተማሪዎች የዚህን ምዕራፍ ይዘቶች ተምራችሁ ካጠናቀቃችሁ በኋላ:-

- የመገኛን ትርጉም ትገልጻላችሁ::
- የአንድን ቦታ አንጻራዊ መገኛዎች ትለያላችሁ::
- የወረዳችሁን አንጻራዊ መገኛ ትገልጻላችሁ::
- የምትኖሩበትን ወረዳ መገኛ ከአጎራባች ወረዳዎች አንፃር ትገልጻላችሁ::
- በወረዳችሁ ዉስጥ የሚገኙትን ቀበሌዎች ስም ትጠቅሳላችሁ::
- ባዘጋጃችሁት ካርታ ላይ የወረዳችሁን ቀበሌዎች ታመለክታላችሁ::
- የአጎራባች ወረዳዎችን ስም ትዘረዝራላችሁ::

## በምዕራፉ የተካተቱ ይዘቶች

1.1 የመገኛ ትርጉም

1.2 የአንጻራዊ መገኛ ትርጉም

1.3 የወረዳችን አንጻራዊ መገኛ

1.4 የአጎራባች ወረዳዎች ስም እና መገኛቸዉ

## መግቢያ

ውድ ተማሪዎች! በአንደኛ ክፍል የአከባቢ ሳይንስ ትምህርት ስለ ቅርብ አካባቢያችሁ ወይም ስለ ቀበሌያችሁ መገኛ ተምራችኋል፡፡ በሁለተኛ ክፍል አከባቢ ሳይንስ ትምህርት ምዕራፍ አንድ ዉስጥ ደግሞ ስለ ወረዳችሁ መገኛ፣ስለመገኛ እና አንጻራዊ መገኛ ትርጉም ፣ ስለሚትኖሩት ወረዳ አንፃራዊ መገኛ ፣ የአጎራባች ወረዳዎች ስም እና አንጻራዊ መገኛቸዉን ትማራላችሁ፡፡

## 1.1. የመገኛ ትርጉም



### ቁልፍ ቃል

- መገኛ

### ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቅ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች

ውድ ተማሪዎች! ይህንን ይዘት ተምራችሁ ካጠናቀቃችሁ በኋላ፡-

- የመገኛን ትርጉም ትናገራላችሁ፡፡
- ቤታችሁ በየትኛዉ ቀበሌ እንደሚገኝ ትገልጻላችሁ፡፡
- ቀበሌያችሁ በየትኛዉ ወረዳ ዉስጥ እንደሚገኝ ትናገራላችሁ፡፡

**የተግባር ክንዋኔ 1.1: የግል ሥራ**

**ዓላማ፡-** የመገኛ ትርጉም መናገር

**መመሪያ፡-** ለሚከተሉት ጥያቄዎች መልስ ስጥ/ጭ፡፡

**ጥያቄዎች፡-**

1. መገኛ ማለት ምን ማለት ነዉ?
2. በመማሪያ ክፍል ዉስጥ የተቀመጥከዉ/ሽዉ የትኛዉ ረድፍ ላይ ነዉ?

መገኛ ማለት አንድ የሆነ ቦታ(ለምሳሌ:ት/ቤት፣ቀበሌ፣ወረዳ፣ወዘተ. በመሬት ላይ ወይም በካርታ ላይ የት እንደሚገኝ የሚያሳይ ነዉ::

መልመጃ 1.1

**መመሪያ:-** ቀጥሎ ለቀረቡት ጥያቄዎች አጭር መልስ ስጥ/ጭ::

1. መኖሪያ ቤታችሁ የሚገኘዉ በየትኛዉ ቀበሌ ነዉ?
2. ትምህርት ቤታችሁ የሚገኝበት ቀበሌ ማን ተብሎ ይጠራል?

## 1.2. የአንጻራዊ መገኛ ትርጉም



**ቁልፍ ቃላት**

- ◆አንጻራዊ መገኛ
- ◆ካርታ

ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቁ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች:-

ዉድ ተማሪዎች! ይህንን ይዘት ተምራችሁ ካጠናቀቃችሁ በኋላ:-

- የአንጻራዊ መገኛ ትርጉም በምሳሌ ታብራራላችሁ::
- ካርታ ምን እንደሆነ ትገልጻላችሁ::

**የተግባር ክንዋኔ 1.2:** የግል ሥራ

**ዓላማ:-** የተቀመጡበትን ቦታ አንጻራዊ መገኛ መናገር::

**መመሪያ:-** ለሚከተሉት ጥያቄዎች መልስ ስጥ/ጭ::

**ጥያቄዎች:-**

1. በመቀመጫህ/ሽ ላይ እንደተቀመጥክ/ሽ ከግራ፣ከፊት፣ከቀኝ እና ከኋላሽ/ህ እነማን እንደተቀመጡ ስም እየጠራችሁ ለመምህራችሁ ተናገሪ/ር:
2. ካርታ ማለት ምን ማለት ነዉ?

ስለ አንጻራዊ መገኛ በቀላሉ ለመግለጽ የተለያዩ መንገዶችን መጠቀም ትችላላችሁ ። በዚህም መሠረት በአንድ ቦታ ቆመን ወይም ተቀምጠን የተለያዩ ነገሮችን ከፊት፣ከኋላ፣ከግራ ወይም ከቀኝ በማለት መገኛቸዉን መግለጽ ወይም ማመልከት እንችላለን። አንጻራዊ መገኛ ማለት አንድን አካባቢ ከሌሎችአካባቢዎች አንጻር መግለጽ ነዉ።

### ካርታ ምንድን ነዉ?

ካርታ ማለት በመሬት ላይ የሚገኙ ልዩ ልዩ ቦታዎችን አነስተኛ በሆነ መጠን በወረቀት ላይ ለማሳየት የሚረዳ ወካይ ስዕል ነዉ።

### መልመጃ 1.2

መመሪያ:-ቀጥሎ ለቀረቡት ጥያቄዎች አጭር መልስ ስጥ/ጭ።

1. የሚከተሉት ቦታዎች ከመማሪያ ክፍላችሁ አንጻር (በቀኝ፣ በግራ፣ ከፊት ወይም ከኋላ በማለት) በየት በኩል እንደሚገኙ ግለጽ/ጭ።

   ሀ. የት/ቤቱ ሰንደቅ ዓላማ

   ለ. የእግር ኳስ ሜዳ

   ሐ. ቤተ-መጽሀፍ

   መ. የተማሪዎች መጸዳጃ ቤት

## 1.3. የወረዳችን አንጻራዊ መገኛ



### ቁልፍ ቃላት

- ◆ወረዳ
- ◆አቅጣጫ

### ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቁ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች

ዉድ ተማሪዎች! ይህንን ይዘት ተምራችሁ ካጠናቀቃችሁ በኋላ:-

- ወረዳ ምን እንደሆነ ታብራራላችሁ።
- አራቱን ዋና ዋና አቅጣጫዎች ትለያላችሁ።
- የወረዳችሁን አንጻራዊ መገኛ ትገልጻላችሁ።

## የተግባር ክንዋኔ 1.3: የግል ሥራ

**ዓላማ**:- የወረዳን አንጻራዊ መገኛ ማብራራት

**መመሪያ**:- ለሚከተሉት ጥያቄዎች መልስ ስጭ/ጥ፡፡


**ጥያቄዎች**:-

1. የወረዳችሁን ስም ጥቀሽ/ስ፡፡
2. የወረዳችሁን ካርታ በመመልከት የወረዳችሁን አንጻራዊ መገኛ አብራሪ/ር፡፡
3. ከወረዳችሁ በሰሜን ፣ በደቡብ ፣ በምስራቅ ወይም በምዕራብ ተፈጥሮአዊ አዋሳኞች አሉ? ካሉ ስማቸዉን ተናገሪ/ር፡፡

### ወረዳ

ወረዳ ማለት በርካታ ቀበሌዎችን የያዘ የአስተዳደር እርከን ሲሆን እያንዳንዱ ወረዳ የራሱ የሆነ ዋና ከተማ አለዉ፡፡ የወረዳችንን አንፃራዊ መገኛ ለመረዳት በቅድሚያ አራቱን አብይ አቅጣጫዎች መለየት ያስፈልጋል፡፡ እነርሱም ምስራቅ፣ ምዕራብ፣ ሰሜን እና ደቡብ ናቸው፡፡

የወረዳችን አንጻራዊ መገኛ ማለት ወረዳችን በአራቱ ዋና ዋና አቅጣጫ ካሉት ተፈጥሮአዊ እና ሰዉ ሰራሽ አዋሳኝ ቦታዎች አንጻር ሲገለጽ የሚገኝበት ቦታ ማለት ነዉ፡፡




ስዕል 1/1 አራቱ ዋና ዋና አቅጣጫዎች

## መልመጃ 1.3

**መመሪያ:-** ቀጥሎ ለቀረቡት ጥያቄዎች አጭር መልስ ስጭ/ጥ፡፡

1. ጠዋት ተነስታችሁ ፊታችሁን ወደ ፀሀይ መውጫ አዙራችሁ በመቆም እጆቻችሁን ወደ ጎንና ጎን ዘርጉ፡፡ በመቀጠልም ቀጥሎ ያሉትን ባዶ ቦታዎች በተገቢ አቀጣጫ ሙሉ፡፡

   ሀ.ግራ እጃችሁ_____________________ያመለክታል፡፡

   ለ.ቀኝ እጃችሁ_____________________ያመለክታል፡፡

   ሐ.ፊታችሁ _____________________ያመለክታል፡፡

   መ.ጀርባችሁ_____________________ ያመለክታል፡፡

## 1.4. የአጎራባች ወረዳዎች ስም እና መገኛቸዉ



**ቁልፍ ቃል**

◆ አጎራባች ወረዳዎች

### ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቁ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች

ዉድ ተማሪዎች! ይህንን ይዘት ተምራችሁ ካጠናቀቃችሁ በኋላ፡-

- የወረዳችሁን አጎራባች ወረዳዎች ስም ትዘረዝራላችሁ፡፡
- የአጎራባች ወረዳዎችን መገኛ ትገልጻላችሁ፡፡
- የወረዳችሁን ካርታ በመንደፍ አንጻራዊ መገኛዉን ከአጎራባች ወረዳ አንጻር ትገልጻላችሁ፡፡

**የተግባር ክንዋኔ 1.4:** የቡድን ዉይይት

**ዓላማ:-**የወረዳቸዉን አጎራባች ወረዳዎች ስም እና አንጻራዊ መገኛ መግለጽ፡፡

**መመሪያ**፡- ስድስት አባላት ያሉት ቡድን መስርታችሁ በእያንዳንዱ ጥያቄ ላይ በመወያየት መልሱ፡፡

**ጥያቄዎች፡-**

1. የወረዳችሁን አጎራባች ወረዳዎች ስም ጥቀሱ፡፡
2. የወረዳችሁን ካርታ በማየት አንጻራዊ መገኛ ግለጹ፡፡
3. የወረዳችሁን ካርታ ከሳላችሁ በኋላ አንጻራዊ መገኛዉን ከአጎራባች ወረዳ አንጻር ግለጹ፡፡

አንጻራዊ መገኛ የሚገለፀዉ በአካባቢያችን በሚገኙ ተፈጥሮአዊ እና ሰዉ ሰራሽ ነገሮች ነዉ፡፡ ተፈጥሮአዊ የምንላቸዉ እንደ ተራራ፣ የዉሃ አካላት (ወንዝ ፣ ሐይቅ፣ኩሬ ወዘተ.) የመሳሰሉት ሲሆኑ ሰዉ ሰራሽ ደግሞ አጎራባች ወረዳዎች ፣ ዞኖች እና የመሳሰሉት ናቸዉ፡፡ የአጎራባች ወረዳዎችን መገኛ ለመለየት ተፈጥሮአዊና ሰዉ ሰራሽ ነገሮችን መጠቀም እንችላለን፡፡

## መልመጃ 1.4

**መመሪያ አንድ፡ ቀጥሎ ለቀረቡት ጥያቄዎች ትክክለኛዉን መልስ ስጭ/ጥ፡፡**

1. የወረዳችሁ አጎራባች ወረዳዎች ስም ዘርዝር/ሪ፡፡
2. ወረዳችሁ ቀጥሎ በቀረቡት አበይት አቅጣጫዎች አንጻር፡-
   - ሀ. በስተሰሜን ከ ________________ ይዋሰናል፡፡
   - ለ.በስተደቡብ ከ ________________ ይዋሰናል፡፡
   - ሐ.በስተምስራቅ ከ________________ ይዋሰናል፡፡
   - መ.በስተምዕራብ ከ ________________ ይዋሰናል፡፡
3. ለጥያቄ ተራ ቁጥር 2 በሰጣችሁት መልስ ላይ ተመስርታችሁ ከወረዳ ችሁ አዋሳኞች ዉስጥ ተፈጥሮአዊ አዋሳኝ የሆነዉን ለይ፡፡

## ማጠቃለያ

- መገኛ ማለት አንድ የሆነ ቦታ ( ለምሳሌ፡-ት/ቤት፣ ቀበሌ፣ ወረዳ፣ወዘተ.) በመሬት ገጽ ላይ የት እንደሚገኝ የሚያሳይ ነዉ፡፡
- አንጻራዊ መገኛ ማለት አንድን አካባቢ ወይም ከሌሎች አካባቢዎች አንጻር መግለጽ ነዉ፡፡
- ካርታ ማለት በመሬት ላይ የሚገኙ ልዩ ልዩ ቦታዎችን አነስተኛ
- በሆነ መጠን በወረቀት ላይ ለማሳየት የሚረዳ ወካይ ስዕል ነዉ፡፡
- ወረዳ ማለት በርካታ ቀበሌዎችን የያዘ የአስተዳደር መዋቅር ነዉ፡፡

## የምዕራፉ ማጠቃለያ ልዩ ልዩ ጥያቄዎች

**መመሪያ አንድ፡- ቀጥሎ የቀረቡትን ዓረፍተ ነገሮች ካነበባችሁ በኋላ ትክክል የሆነዉን "እዉነት"ትክክል ያልሆነዉን "ሐሰት" በማለት መልሽ/ስ፡፡**

1. አንጻራዊ መገኛ የአንድን ቦታ መገኛ ለማወቅ ይጠቅማል፡፡
2. ሰዉ ሰራሽ አዋሳኞች የአንድን ቦታ አንጻራዊ መገኛ ለመግለጽ ይጠቅማሉ፡፡
3. ወረዳ በቀበሌ ዉስጥ የሚገኝ የአስተዳደር መዋቅር ነዉ፡፡
4. የአንድን ቦታ መገኛ ለማወቅ አቅጣጫዎችን ማወቅ አይጠቅምም፡፡

**መመሪያ ሁለት፡- ለሚከተሉት ጥያቄዎች ከተሰጡት አማራጮች ትክክለኛዉን መልስ የያዘዉን ሆሄ ምረጥ/ጭ፡፡**

1. ከሚከተሉት ዉስጥ ተፈጥሮአዊ አዋሳኝ የሆነዉ የቱ ነዉ?

   ሀ. ወረዳ　　　　ሐ. መንገድ

   ለ.ዞን　　　　መ. ወንዝ

2. ከሰዉ ልጅ የዕለት ተዕለት ኑሮ ጋር ከፍተኛ ቁርኝት ያለዉ ሰዉ ሰራሽ ነገር የቱ ነዉ?

ሀ. ሐይቅ ሐ. ትምህርት ቤት

ለ. ተራራ መ. ወንዝ

3. የአንድን ወረዳ አንጻራዊ መገኛ ለመግለጽየማንጠቀመዉ የቱ ነዉ?

ሀ. አየር ሐ. ክልል

ለ. ወረዳ መ.ወንዝ

**መመሪያ ሦስት፡ ለሚከተሉት ጥያቄዎች አጭር መልስ ስጥ/ጭ፡፡**

1. ጠዋት ተነስታችሁ ፊታችሁን ወደ ፀሀይ መግቢያ አዙራችሁ በመቆም እጆቻችሁን ወደ ጎንና ጎን ዘርጉ፡፡ በመቀጠልም ቀጥሎ ያሉትን ባዶ ቦታዎች በተገቢ አቅጣጫ ሙሉ፡፡
   ሀ. ግራ እጃችሁ________________________ያመለክታል፡፡
   ለ. ቀኝ እጃችሁ________________________ያመለክታል፡፡
   ሐ. ፊታችሁ____________________________ያመለክታል፡፡
   መ. ጀርባችሁ__________________________ያመለክታል፡፡
2. የወረዳችሁ ስም________ሲሆን ዋና ከተማዉ____________ ይባላል፡፡
3. በመሬት ላይ የሚገኙ ልዩ ልዩ ቦታዎችን በአነስተኛ መጠን ወረቀት ላይ ለማሳየት የሚረዳ ወካይ ስዕል________________ይባላል፡፡

# ምዕራፍ ሁለት

# ሳይንስን ማስተዋወቅ

## ከምዕራፉ የሚጠበቁ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች

ተማሪዎች የዚህን ምዕራፍ ይዘቶች ተምራችሁ ካጠናቀቃችሁ በኋላ:-

- የዉጫዊ ሰዉነት ክፍሎችን ትለያላችሁ::
- የስሜት ሂዋሳት ጠቀሜታቸዉን ትዘረዝራላችሁ::
- የቁሶችን አካላዊ ባህሪያት ትለያላችሁ::
- የብርሃን ምንጮችን ትዘረዝራላችሁ::

## በምዕራፉ የተካተቱ ይዘቶች

2.1 ዉጫዊ የሰዉነት ክፍሎቻችን እና የስሜት ሕዋሳት

2.1.1 ዉጫዊ የሰዉነት ክፍሎቻችን

.1.2 የስሜት ሕዋሳት እና ጥቅሞቻቸዉ

2.2 የቁሶች አካላዊ ባሕሪያት

2.3 የብርሃን ምንጮች

## መግቢያ

ሰዉነታችን ልዩ ልዩ ክፍሎች አሉት፡፡ የሰዉነት ክፍሎቻችን በሁለ ትመመደብ የሚቻል ሲሆን እነሱም ዉጫዊ እና ዉስጣዊ የሰዉነት ክፍሎች በመባል ይታወቃሉ፡፡ በዚህ ምዕራፍ ስለ ዉጫዊ የሰዉነት ክፍሎች ፣ ስለ ስሜት ሕዋሳት ተግባር፣ ስለ ቁሶች አካላዊ ባሕሪያት እና ስለብርሃን ምንጮች ትማራላችሁ፡፡

## 2.1. ዉጫዊ የሰዉነት ክፍሎቻችንና የስሜት ሕዋሳት

### 2.1.1. ዉጫዊ የሰዉነት ክፍሎቻችን



ቁልፍ ቃል

◆የሰዉነት ክፍሎች

**ከንዑስ ርዕስ የሚጠበቅ አጥጋቢ የመማር ብቃት**

ዉድ ተማሪዎች !ይህንን ይዘት ተምራችሁ ካጠናቀቃችሁ በኋላ፡-

- ዉጫዊ የሰዉነት ክፍሎችን ትዘረዝራላችሁ፡፡

**የንዑስ ርዕስ ይዘት**

- ዉጫዊ የሰዉነት ክፍሎች

## የተግባር ክንዋኔ 2.1: የጥንድ ዉይይት


**ዓላማ**:- ዉጫዊ የሰዉነት ክፍሎችን መዘርዘር

*መመሪያ*:- ቀጥሎ በቀረበዉ ጥያቄ ላይ ከተወያያችሁ በኋላ መልስ አቅርቡ፡፡

**ጥያቄ**:-

1. ዉጫዊ የሰዉነት ክፍሎች የሚባሉት የትኞቹ ናቸዉ?

ዉጫዊ የሰዉነት ክፍሎች የሚባሉት በሰዉነት ዉጫዊ ገጽታ ላይ የሚገኙ የሰዉነት ክፍሎች ናቸዉ፡፡




ስዕል 2/1 ዉጫዊ የሰዉነት ክፍሎች

## 2.1.2. የስሜት ሕዋሳት እና ጥቅሞቻቸዉ



**ቁልፍ ቃል**

◆የስሜት ሕዋሳት

### ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቁ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች

**ይህንን ይዘት ተምራችሁ ካጠናቀቃችሁ በኋላ፡-**

- የስሜት ሕዋሳትን ትለያላችሁ፡፡
- የስሜት ሕዋሳትን ጥቅም ትናገራላችሁ፡፡

### የንዑስ ርዕስ ይዘቶች

◆የስሜት ሕዋሳት

◆ዓይን

◆ጆሮ

◆አፍንጫ

◆ምላስ

◆ቆዳ

### የስሜት ሕዋሳት

**የተግባር ክንዋኔ 2.2: የግል ሥራ**

**ዓላማ**፡- የስሜት ሕዋሳትን መዘርዘር፡፡

**መመሪያ**፡- ለሚከተለዉ ጥያቄ  መልስ ስጥ/ጭ፡፡

**ጥያቄ**፡-

1. የስሜት ሕዋሳትን ዘርዝሪ/ር፡፡

ሰዉነታችን የዉጫዊዉን አካባቢ ለዉጦች መለየት የሚችለዉ በስሜት ሕዋሳት አማካኝነት ነዉ ፡፡ የስሜት ሕዋሳት የሚባሉት ዓይን ፣ጆሮ፣ አፍንጫ፣ ምላስ እና ቆዳ ናቸዉ፡፡

### ዓይን

## የተግባር ክንዋኔ 2.3: የግል ሥራ

**ዓላማ** ፡- የዓይንን ተግባር መግለጽ፡፡ ዓይንን ለጉዳት የሚዳርጉ ድርጊቶችን እና መከላከያ መንገዶችን መዘርዘር፡፡

**መመሪያ**፡- ለሚከተሉት ጥያቄዎች መልስ ስጥ_ጭ፡፡

**ጥያቄዎች**፡-

1. ዓይን ለምን ይጠቅማል?
2. ዓይንን ለጉዳት የሚዳርጉ ነገሮች(ድርጊቶችን) ዘርዝር/ሪ፡፡
3. በዓይናችን ላይ ጉዳት እንዳይደርስ እንዴት እንከላከላለን?

ዓይን ለማየት የሚያገለግል የስሜት ሕዋስ ነዉ፡፡ ዓይናችን ማየት የሚችለዉ ብርሃን ባለበት አካባቢ ነዉ፡፡ ዓይናችን ብርሃን ሲኖር የቀለም ዓይነቶችን፣ልዩ ልዩ ነገሮችን ለመለየትና ርቀት ለመገመት ይረዳናል፡፡ ዓይናችንን ለጉዳት የሚዳርጉት ነገሮች አቧራ ፣

ጭስ ፣ ከፍተኛ የብርሃን ጨረር በቆሻሻ እጅ መንካት እና ደብዛዛ ብርሃን ባለበት ቦታ ደብተር ወይም መጽሀፍ ማንበብ የመሳሰሉት ናቸዉ፡፡



ስዕል 2/2 ዓይን ለማየት ይጠቅማል

## ጆሮ

### የተግባር ክንዋኔ 2.4: የቡድን ዉይይት

**ዓላማ** :- የጆሮን ተግባር መግለጽ፡፡

-ለጆሮ መደረግ የሚገባዉን ጥንቃቄ መናገር ፡፡

**መመሪያ**:- ለሚከተሉት ጥያቄዎች ማብራሪያ ስጡ፡፡

**ጥያቄዎች**:-

1. ጆሮ ለምን ይጠቅማል?
2. ለጆሮአችን መደረግ ያለበትን ጥንቃቄዎች ዘርዝሩ፡፡

ጆሮአችን የተለያዩ ድምጾችን ለመስማት የሚያገለግል የስሜት ህዋስ ነዉ፡፡ ስለሆነም የጆሮአችንን ንጽህና መጠበቅና ጉዳት እንዳይደርስበት ጥንቃቄ ማድረግ አለብን፡፡ ጆሮአችንን ዘወትር በንጹህ ዉሃና ሳሙና ከመታጠብ ዉጪ ዉስጡን መጎርጎር የለብንም፡፡ ከፍተኛ ድምጽ በጆሮ ላይ ጉዳት ስለሚያስከትል የድምፅ ብክለት ካለበት አካባቢ መራቅ ይገባናል፡፡



ስዕል 2/3 ጆሮ ለመስማት ይጠቅማል

## አፍንጫ

### የተግባር ክንዋኔ 2.5: የጥንድ ዉይይት

**ዓላማ**:- የአፍንጫ ጠቀሜታዎችን መዘርዘር፡፡

**መመሪያ**:-ለሚከተሉት ጥያቄዎች ማብራሪያ ስጡ፡፡

**ጥያቄዎች**:-

1. በአፍንጫችሁ መለየት የምትችላ*ቸዉን የሽታ ዓይነቶች ዘርዝሩ፡፡
2. አፍንጫን በእጅ መነካካት መጥፎ ልማድ ነዉ የሚባለዉ ለምንድን ነዉ?

አፍንጫችን ለማሽተት የሚጠቅም የስሜት ሕዋስ ነዉ፡፡ ስለዚህ የአፍንጫችን የማሽተት ስራ እንዳ ይስተጓጎል ንጽህናዉን መጠበቅና ጉዳት እንዳይደርስበት ጥንቃቄ ማድረግ አለብን ፡፡ ዉድ ተማሪዎች! የተገኘዉን ነገር ሁሉ ማሽተት ለአደጋ ስለሚያጋልጥ ጥንቃቄ ማድረግ አለባችሁ፡፡



ስዕል 2/4 አፍንጫ ለማሽተት ይጠቅማል

**ምላስ**

## የተግባር ክንዋኔ 2.6: የቡድን ዉይይት

**ዓላማ**:- የምላስን ጥቅም መግለጽ፡፡

- በምላሳቸዉ ያልተገቡ ነገሮችን መቅመስ ጉዳትእንዳለዉ መናገር፡፡

**መመሪያ**:-ስድስት አባላት ያሉት ቡድን መስርታችሁ በእያንዳንዱ ጥያቄ ላይ በመወያየት መልስ አቅርቡ፡፡

**ጥያቄዎች**:-

1. የምላስ ጥቅም ምንድን ነዉ?
2. ምግብ ነክ ከሆኑ ንጹህ ነገሮች ዉጪ ሌሎች ነገሮችን በምላስ እንድንቀምስ የማይመከረዉ ለምንድን ነው?

ምላስ ለመቅመስ የሚያገለግል የስሜት ሕዋስ ነዉ፡፡ የተለያዩ ምግቦችን ለምሳሌ፡ የሎሚ፣ የብቱካን ፣ የጨዉ፣ የስኳር እና የመሳ ሰሉትን ጣዕማቸዉን መለየት የምንችለዉ በምላሳችን ቀምሰን ነዉ፡፡ ይሁን እንጂ የተገኘዉን ነገር ሁሉ ወደ አፍ በመዉሰድ በምላስ ለመቅመስ መሞከር አይመከርም ምክንያቱም አደጋ ልያስከትል ስለሚችል፡፡ ጣፋጭ፣ ኮምጣጣ፣ መራራ፣ ጨዋማ ፣ ወዘተ. ምላሳችን በመቅመስ ከሚለያቸዉ ጣዕሞች መካከል የሚጠቀሱ ናቸዉ፡፡



ስዕል 2/5 ምላስ ለመቅመስ ይረዳል

**ቆዳ**

## የተግባር ክንዋኔ 2.7: የቡድን ወይይት

**ዓላማ፡-** የቆዳን ጥቅም መግለጽ፡፡


- ቁሶችን በመዳሰስ ሻካራ ፣ ልሙጥ ፣ ሹል ፣ ዱልዱም መሆኑን መለየት፡፡

**መመሪያ፡-** ለሚከተሉት ጥያቄዎች ማብራሪያ ስጡ፡፡

**ጥያቄዎች፡-**

1. ቆዳችን ለምን ይጠቅማል?
2. ከፊታችሁ ያለዉን ጠረጴዛ በእጃችሁ መዳፍ በመዳሰስ ሻካራ ወይም ልሙጥ መሆኑን ለይታችሁ ተናገሩ፡፡
3. የእስክርብቶአችሁን ጫፎች ተራ በተራ በመዳሰስ ሹል የሆነዉን እና ዱልዱም የሆነዉን ጫፍ ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡

ቆዳ ለመዳሰስ የሚጠቅም የስሜት ሕዋስ ነዉ፡፡ በእጅ በመዳሰስ ወይም በመንካት አንድ ቁስ ልሙጥ ወይም ሻካራ፣ ሹል ወይም ዱል ዱም፣ ሞቃት ወይም ቀዝቃዛ፣ ወዘተ. መሆኑን ለመለየት እንችላለን፡፡





ስዕል 2/6 እጅ ለመዳሰስ እና ሙቀትን ለመለየት ያስችላል

## መልመጃ 2.1

*መመሪያ፡- ለሚከተሉት ጥያቄዎች መልሽ/ስ፡፡*

1. ከዚህ በታች ያለውን የሰው ሥዕል በመመልከት በቁጥር የተመለከቱትን የሰውነት ክፍሎችን ስም ተናገሪ/ር ፡፡




ስዕል 2/7 ዉጫዊ የሰዉነት ክፍሎች

2. ቀጥሎ ባለዉ ሰንጠረዥ ዉስጥ የቀረቡት ዉጫዊ የሰዉነት ክፍሎች በአንድ ሰዉ ላይ ብዛታቸዉ ስንት እንደሆነ ጥቀሱ፡፡

| ዉጫዊ የሰዉነት ክፍል | ብዛት |
|---|---|
| 1. ዓይን | |
| 2. ጆሮ | |
| 3. የእጅ ጣት | |
| 4. እጅ | |
| 5. እግር | |
| 6. አፍንጫ | |

3. ቀጥሎ የቀረቡትን ስሜት ሕዋሳት ስም በተሰጠዉ ባዶ ቦታ ሙሉ፡፡

**የስሜት ሕዋስ ስም የስሜት ሕዋስ ስም**



ሀ______



መ______



ለ ______



ሠ ______



ሐ ______

ስዕል 2/8 የስሜት ህዋሳት

## 2.2. የቁሶች አካላዊ ባሕሪያት



**ቁልፍ ቃላት**

- ቁስ
- ቀለም
- መጠን
- ሸካራ
- ቅርጽ
- ልሙጥ

### ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቁ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች

ዉድ ተማሪዎች!ይህንን ይዘት ተምራችሁ ካጠናቀቃችሁ በኋላ፡-

- የቁስ ምንነት ታብራራላችሁ፡፡
- የቁሶችን አካላዊ ባህሪያት ትዘረዝራላችሁ፡፡

### ቁስ

**የተግባር ክንዋኔ 2.8: የቡድን ዉይይት**

**ዓላማ**፡- የቁስን ምንነት መግለጽ፡፡

**መመሪያ**፡ ስድስት አባላት ያሉት ቡድን መስርታችሁ ቀጥሎ ባለዉ ጥያቄ ላይ በመወያየት ዘገባ አቅርቡ፡፡

**ጥያቄ**፡-

1. ቁስ ምንድን ነዉ? ምሳሌ በመስጠት አብራሩ፡፡

ቁስ ማለት ማንኛዉም በአካባቢያችን የሚገኝ ተፈጥሮአዊ እና ሰዉ ሰራሽ ነገር ሲሆን ለሰዉ ልጆች በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ጥቅም የሚሰጥ ነዉ ፡፡ በተፈጥሮ የሚናገኛቸዉ ቁሶች ድንጋይ ፣ ጥጥ፣ እንጨት፣ ዉሃ ፣ አፈር፣ ወዘተ. ሲሆኑ ሰዉ ሰራሽ የምንላቸዉ ደግሞ ጎማ፣ ብርጭቆ

፣ ጨርቅ፣ ፐላስቲክ ፣ ወዘተ. ናቸዉ።

## የቁስ አካላዊ ባህሪያት

### የተግባር ክንዋኔ 2.9: የቡድን ዉይይት

**ዓላማ**፡- የቁስን አካላዊ ባህሪያት መዘርዘር።

**መመሪያ**፡- ስድስት አባላት ያሉት ቡድን መስርታችሁ ቀጥሎ በቀረበዉ ጥያቄ ላይ በመወያየት ዘገባ አቅርቡ።

**ጥያቄ**፡-

1.የቁስ አካላዊ ባህሪያትን ዘርዝሩ።

በዙሪያችን ያሉ ቁሶች የተለያየ አካላዊ ባህርይ አላቸዉ። ስለዚህ ከአካላዊ ባህሪያቸዉ አንጻር ቁሶችን በቀለም፣በቅርፅ፣በመጠን፣በሸካ ራነት ወዘተ. ለያይተን እንመድባቸዋለን።

**ሀ.ቁሶችን በቀለም መመደብ፡-** ቁሶችን ዉጫዊ ቀለማቸዉን በመመልከት ቀይ ፣ነጭ፣ ጥቁር፣ ቢጫ ወዘተ. በማለት መለየት ይቻላል። ለምሳሌ፡- ጥሬ ወተት ነጭ ቀለም አለዉ።

**ለ. ቁሶችን በቅርፃቸዉ መመደብ፡-** ቁሶች ባላቸዉ ቅርፅ እንደሚከተለዉ መመደብ ይቻላል ማለትም ጠፍጣፋ፣ ሹል፣ ክብ ፣ሞላላ ወዘተ ፡ ፡ ለምሳሌ፡- የእስክብሪቶ ጫፍ ሹል ነዉ።

**ሐ.ቁሶችን በመጠናቸዉ መመደብ፡-** ቁሶች ባላቸዉ መጠን እንደሚከተለዉ መመደብ ይቻላል፤ማለትም ወፍራምና ቀጭን ፤ትልቅና ትንሽ፤ሰፊና ጠባብ ወዘተ. ለምሳሌ፡-ላም ትልቅ ሲሆን ዶሮ ትንሽ ነዉ ።

መ. ቁሶች ባለቸዉ ዉጫዊ ገጽታ ሸካራ እና ልሙጥ ተብለዉ ለሁለት ይከፈላሉ ለምሳሌ፡- ጥቁር ሰሌዳ ልሙጥ ሲሆን አሸዋ ሸካራ ነዉ።

## መልመጃ 2.2

**መመሪያ: ቀጥሎ ለቀረቡት ጥያቄዎች መልስ ስጥ/ጭ::**

1. በአካባቢያችሁ የሚገኙትን ቁሶች ከዘረዘራችሁ በኋላ ተፈጥሮዊ እና ሰዉ ሰራሽ በማለት ለይ/ዪ::
2. በአካባቢያችሁ የሚገኙትን ቁሳ ቁስ ባህሪያትን በመለየት ቀጥሎ በቀረበዉ ምሳሌ መሰረት በሰንጠረዥ ዉስጥ መዝግበህ/ሽ ለመምህሩ አሳዩ/ይ::

| ሸካራ | ልሙጥ | ክብ | ጠፍጣፋ | ሹል | ወፍራም | ቀጭን | ቀይ | ጥቁር |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ጡብ | ወረቀት | ኳስ | ወለል | ጦር | ዝሆን | ጥንቅሽ | ደም | ከሰል |
| | | | | | | | | |
| | | | | | | | | |

## 2.3. የብርሃን ምንጮች



**ቁልፍ ቃላት**

◆ብርሃን ◆የብርሃን ምንጭ

### ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቁ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች

**ዉድ ተማሪዎች!ይህንን ይዘት ተምራችሁ ካጠናቀቃችሁ በኋላ:-**

- ብርሃን ምን እንደሆነ ታብራራላችሁ::
- የብርሃን ምንጮችን ትለያላችሁ::

## የብርሃን ምንጭ

**የተግባር ክንዋኔ 2.10: የቡድን ዉይይት**

**ዓላማ**:- የብርሃን ምንጮችን መለየት

**መመሪያ**:- ስድስት አባላት ያሉት ቡድን መስርታችሁ ቀጥሎ ባለዉ ጥያቄ ላይ በመወያየት መልስ አቅርቡ፡፡

**ጥያቄ**:- ብርሃን ከየት ይገኛል?

ብርሃን በአከባቢያችን ያሉ ነገሮችን በዓይናችን እንድናይ የሚያደርግ ሀይል ነዉ፡፡ የብርሃን ምንጮች በሁለት ሲከፈሉ እነርሱም ተፈጥሮአ ዊና ሰዉ ሰራሽ ይባላሉ፡፡ ተፈጥሮአዊ የብርሃን ምንጮች የሚባሉት ፀሀይ፣ ጨረቃ፣ ክዋክብት፣ ወዘተ. ናቸዉ፡፡








ስዕል 2/9 ተፈጥሮአዊ የብርሃን ምንጮች

## ሰዉ ሰራሽ የብርሃን ምንጮች

ሰዉ ሰራሽ የብርሃን ምንጮች የሚባሉት እንደ ኩራዝ፣ ፋኖስ፣ ሻማ፣ ባትሪ፣ ኮሬንቲ(ኤለክትሪክ)፣የመሳሰሉት ናቸዉ፡፡




ስዕል2/10 ሰዉ ሰራሽ የብርሃን ምንጮች

## መልመጃ 2.3

*መመሪያ:- ለሚከተሉት ጥያቄዎች አጫጭር ማብራሪያ ስጥ/ጭ።*

1. የብርሃን ጥቅም ምንድን ነዉ?
2. ተፈጥሮአዊ የብርሃን ምንጮችን ዘርዝሪ/ር።
3. በአካባቢያችሁ የሚገኙትን ሰዉ ሰራሽ የብርሃን ምንጮችን ጥቀሽ/ስ።

## ማጠቃለያ

- ዉጫዊ የሰዉነት ክፍሎች የምንላቸዉ በሰዉነት ዉጫዊ ገጽታ ላይ የሚገኙ እና በማየት የምንለያቸዉ ናቸዉ።
- ሰዉነታችን የዉጫዊዉን አካባቢ ለዉጦች መለየት የሚችለዉ በስሜት ሕዋሳት አማካኝነት ነዉ።
- ቁስ ማለት በተፈጥሮ ወይም በሰዉ ሰራሽ የሚገኝ ነገር ሲሆንለ ሰዉ ልጅ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ጥቅም የሚሰጥ ነዉ።
- ከአካላዊ ባህሪያቸዉ አንጻር ቁሶችን በቀለም፣በቅርጽ ፣ በመጠን እና በሸካራነትወዘተ. በማለትእንለያቸዋለን።
- የብርሃን ምንጮች ተፈጥሮአዊ እና ሰዉ ሰራሽ በመባል ለሁለት ይከፈላሉ።

## የምዕራፉ ማጠቃለያ ጥያቄዎች

**መመሪያ አንድ፡-ቀጥሎ የቀረቡትን ዓረፍተ ነገሮች አንብባችሁ ትክክል የሆነዉን "እዉነት" ትክክል ያልሆነዉን "ሐሰት" በማለት መልሽ/ስ።**

1. ያለ ብርሃን ዓይናችን ቀለማትን መለየት ይችላል።
2. ጆሮን በሹል ነገር መጎርጎር ጥሩ ልማድ ነዉ።
3. ቀዝቃዛ ወይም የሞቀ ነገር የምንለየዉ በዓይናችን ነዉ።
4. በአካባቢያችን የሚገኙ ቁሶች በሙሉ ተፈጥሮአዊ ብቻ ናቸዉ።

**መመሪያ ሁለት፡-ለሚከተሉት ጥያቄዎች ከተሰጡት አማራጮች ትክክለኛዉን መልስ የያዘዉን ሆሄ ምረጭ/ጥ።**

1. ከአንገት በላይ የሚገኝ የሰዉነት ክፍል የትኛዉ ነዉ?
   ሀ. ወገብ  
   ለ. ሆድ  
   ሐ.ጆሮ  
   መ.ጉልበት
2. ለመቅመስ የሚጠቅም የስሜት ሕዋስ የትኛዉ ነዉ?
   ሀ. ጆሮ  
   ለ. አፍንጫ  
   ሐ.ዓይን  
   መ. ምላስ
3. ለማሽተት የሚጠቅም የስሜት ሕዋስ የትኛዉ ነዉ?
   ሀ. ምላስ  
   ለ. አፍንጫ  
   ሐ. ዓይን  
   መ. ጆሮ
4. ተፈጥሮአዊ የብርሃን ምንጭ የሆነዉ የትኛዉ ነዉ?
   ሀ. ኤለክትሪክ  
   ለ.ጨረቃ  
   ሐ. ፋኖስ  
   መ. ባትሪ
5. ቀን ብርሃን የሚሰጠን ተፈጥሮአዊ የብርሃን ምንጭ የትኛዉ ነዉ?
   ሀ. ባትሪ  
   ለ. ሃይ  
   ሐ.ጨረቃ  
   መ. አምፖል
6. ከሚከተሉት ዉስጥ ሸካራ የሆነዉ የትኛዉ ነዉ?
   ሀ. ጥቁር ሰሌዳ  
   ለ. መስተዋት  
   ሐ. ንጹህ ዉሃ  
   መ. ጣዉላ

7. ከሚከተሉት ዉስጥ ሹል የሆነዉ  የቱ ነዉ?

ሀ. ብርጭቆ
ሐ. መርፌ
ለ. ጎማ
መ.ፕላስቲክ ከረጥት

8. የወተትን ቀለም የሚለየዉ  የስሜት ሕዋስ የትኛዉ ነዉ?

ሀ. ቆዳ
ሐ. አፍንጫ
ለ.ምላስ
መ. ዓይን

9. ድምጽ ለመስማት የሚያገለግል የስሜት ሕዋስ የትኛዉ ነዉ?

ሀ. ዓይን
ለ. ጆሮ
ሐ. ምላስ
መ. እጅ

# ምዕራፍ ሦስት

# የተፈጥሮ አካባቢያችን

## ከምዕራፉ የሚጠበቁ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች

ተማሪዎች የዚህን ምዕራፍ ይዘቶች ተምራችሁ ካጠናቀቃችሁ በኋላ:-

- የአየር ሁኔታን እንደ ዕለቱ አየር ፀባይ ትገልጻላችሁ::
- ለአየር ሁኔታ ምሳሌ ትሰጣላችሁ::
- የአየር ንብረትን እንደ ረጅም ጊዜ አማካይ የአየር ሁኔታ ትገልጻላችሁ::
- የወረዳችሁን አማካይ የዝናብ መጠን በቀላል ባር ግራፍ ታሳያላችሁ::
- የአየር ንብረት እንዴት በሕይወታችሁ ላይ ተጽእኖ እንደሚያሳድር ታብራራላችሁ::
- በአካባቢያችሁ በብዛት የሚገኙትን እፅዋት ትለያላችሁ::
- ለእ}ዋት ዕድገት አስፈላጊ የሆኑ ነገሮችን ትዘረዝራላችሁ::
- የእ}ዋትን ልዩ ልዩ ጥቅሞች ትዘረዝራላችሁ::
- ለእንስሳት በሕይወት መኖር አስፈላጊ የሆኑ ነገሮችን ትዘረዝራላችሁ::
- እንስሳትን ትመድባላችሁ::
- እንደገና ጥቅም ላይ መዋል የሚችሉትን እና ለፋብሪካ ጥሬ ዕቃ መሆን የሚችሉትን ቁሳቁሶች ትለያላችሁ::
- ባህላዊ መንገድ በመጠቀም ከቆሻሻ ወይም ከተጣሉ ቁሳቁሶች ምን ሊሠራ እንደሚችል ትናገራላችሁ::

## በምዕራፉ የተካተቱ ይዘቶች

3.1 የአየር ሁኔታ እና የአየር ንብረት
3.2. በወረዳችን ውስጥ የሚገኙ እፅዋት
3.3. በወረዳችን ውስጥ የሚገኙ እንስሳት
3.4. በወረዳችን ውስጥ የሚገኙ የተፈጥሮ ሀብቶች
3.5. አከባቢያችንን መንከባከብ

## መግቢያ

የተፈጥሮ አካባቢ ማለት ሕይወት ያላቸዉንና ሕይወት የሌላቸዉን ነገሮች አካትቶ የያዘ እና እንደ ዝናብ፣ንፋስ ፣ ሙቀት፣ቅዝቃዜ ፣ ብርሃን ፣ ጨለማ ያሉ ተለዋዋጭ ክስተቶች የሚንጸባረቁበት ሥፍራ ነዉ፡፡ በመሆኑም በዚህ ምዕራፍ የአየር ሁኔታ፣ የአየር ንብረት፣ በወረዳችሁ ዉስጥ የሚገኙ እፅዋትና እንስሳት ፣ በወረዳችሁ ዉስጥ የሚገኙ የተፈጥሮ ሀብቶች እና የአከባቢያችሁን እንክብካቤ ትማራላችሁ፡፡

## 3.1. የአየር ሁኔታ እና የአየር ንብረት



### ቁልፍ ቃላት

- የአየር ሁኔታ
- የአየር ንብረት

### ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቁ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች

ዉድ ተማሪዎች!ይህንን ይዘት ተምራችሁ ካጠናቀቃችሁ በኋላ፡-

- የአየር ሁኔታን ትገልጻላችሁ፡፡
- የአየር ንብረትን ምሳሌ በመስጠት ታብራራላችሁ፡፡
- ቀለል ያለ ባር- ግራፍ በመሥራት የወረዳችሁን ዋና ዋና የዝናብ ወራት ታሳያላችሁ፡፡
- የሰራችሁትን ባር ግራፍ በማየት የበለጠ ዝናብ የሚያገኙ ወራት

የትኞቹ እንደሆኑ ትተነትናላችሁ።

- በአየር ሁኔታ እና በአየር ንብረት መካከል ያለዉን ልዩነት ትገልጻላችሁ ።

## የንዑስ ርዕስ ይዘቶች

- የአየር ሁኔታ
- የአየር ንብረት

### የአየር ሁኔታ

**የተግባር ክንዋኔ 3.1: የግል ሥራ**

**ዓላማ**:- የዕለቱን የአየር ሁኔታ መለየት

**መመሪያ**:- ለሚከተሉት ጥያቄዎች ማብራሪያ ስጥ/ጭ ።

**ጥያቄዎች**:-

1. ዉድ ተማሪዎች! ወደ ትምህርት ቤት ስትመጡ እና ስትመለሱ ባለዉ የአየር ሁኔታ መካከል ልዩነት አለ? ማብራሪያ ስጥ/ጭ።
2. ወፍራም እና ስስ ልብሶችን የሚትለብሱበት የአየር ሁኔታዉ ምን ዓይነት ሲሆን ነዉ?

የአየር ሁኔታ በአንድ አካባቢ ላይ የሚታይ የዕለቱ (የ24 ሰዓት) የአየር ፀባይ ነዉ። የአንድን አካባቢ ዕለታዊ የአየር ሁኔታ ፀሀያማ ፣ ዝናባማ ፣ ነፋሻ ፣ ወዘተ. በማለት መግለጽ እንችላለን። በአንድ ዕለት ዉስጥ ያለዉ የአየር ሁኔታ ተለዋዋጭ ነዉ።







ስዕል 3/1 የአየር ሁኔታ በከፊል

## የአየር ንብረት

### የተግባር ክንዋኔ 3.2: የቡድን ዉይይት

**ዓላማ**:-የአየር ንብረትን መግለጽ፡፡


-በአየር ንብረት ለዉጥ ምክንያት የሚመጡ ችግሮችን መዘርዘር፡፡

**መመሪያ**:- ስድስት አባላት ያሉት ቡድን መስርታችሁ ቀጥሎ ባሉት ጥያቄዎች ላይ በመወያየት ዘገባ አቅርቡ፡፡

**ጥያቄዎች**:-

1. የአየር ንብረት ምንድን ነዉ?
2. የአየር ንብረት ለዉጥ ምን ዓይነት ችግሮችን ያስከትላል?

የአየር ንብረት ማለት የአንድ አካባቢ የረጅም ጊዜ አማካይ የአየር ሁኔታ ማለት ነዉ፡፡ ለምሳሌ ቀጥሎ ያለዉ ባር ግራፍ የአንድን ቦታ የረጅም ጊዜ አማካይ የዝናብ መጠን የሚያሳይ ነዉ፡፡




ስዕል 3/2 አማካይ የዝናብ መጠን (በሚ.ሜ)

ምቹ የአየር ንብረት ለሰዉ ልጅ ኑሮ በጣም አስፈላጊ ነዉ፡፡ እንዲሁም እፅዋትእና ሌሎች እንስሳትም ለመኖር ተስማሚ የአየር ንብረት ይፈልጋሉ፡፡ የአየር ንብረት ለዉጥ በሰዉ ልጅ ሕይወት እና ኑሮ ላይ አዳዲስ ችግሮችን በማስከተል ላይ ይገኛል፡፡

## መልመጃ 3.1

**መመሪያ 1:-ቀጥሎ ለቀረቡ ጥያቄዎች መልስ ስጥ/ጭ::**

1. ደመናማ፣ ፀሀያማ ወይም ዝናባማ የሚለዉ ምንን ይገልጻል?
2. የረጅም ጊዜ አማካይ የአየር ሁኔታ ምን ይባላል?
3. ዉድ ተማሪዎች!ቀላል ባር- ግራፍ በመሥራት:-
 ሀ. የወረዳችሁን ዋና ዋና የዝናብ ወራት አሳዩ/ይ::
 ለ. የበለጠ ዝናብ የሚያገኙ ወራትን ተንትኝ/ን::
4. ደጋ፣ ወይናደጋ ፣ ቆላ ስንል የአካባቢዉን ምን እየገለጽን ነዉ?
5. የአየር ንብረት ለዉጥ የሚያስከትላቸዉን ችግሮች ዘርዝሪ_ር::

## 3.2. በወረዳችን ዉስጥ የሚገኙ እፅዋት

### 3.2.1. እፅዋት



**ቁልፍ ቃል**

◆ እፅዋት

**ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቁ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች**

ዉድ ተማሪዎች!ይህንን ይዘት ተምራችሁ ካጠናቀቃችሁ በዃላ:-

- በወረዳችሁ የሚገኙ እፅዋቶችን ትዘረዝራላችሁ::
- በወረዳችሁ በብዛት የሚገኘዉን እፅዋት ለዩ::

**እፅዋት**

**የተግባር ክንዋኔ 3.3: የቡድን ዉይይት**

**ዓላማ**:- በወረዳቸዉ የሚገኙ እዋት መዘርዘር::

- በወረዳቸዉ ለምግብነት የሚዉሉ እፅዋትን መለየት

**መመሪያ፡-** ስድስት አባላት ያሉት ቡድን መስርታችሁ ቀጥሎ ባሉት ጥያቄዎች ላይ በመወያየት መልስ አቅርቡ፡፡

**ጥያቄዎች፡-**

1. በወረዳችሁ የሚገኙ እፅዋት ስማቸዉን ዘርዝሩ፡፡
2. በወረዳችሁ በብዛት የሚገኙ እፅዋቶችን ለዩ፡፡
3. በወረዳችሁ ለምግብነት ጥቅም ላይ የሚዉሉ እፅዋቶችን ለዩ፡፡

በወረዳችንም ሆነ በሌሎች አካባቢዎች የሚገኙ እፅዋት ባላቸዉ መሠረታዊ የሕይወት ሂደት (በማደግ ፣ በመተንፈስ ፣ ምግብ በማዘጋጀት ፣ መራባት በመቻላቸዉ ፣ ወዘተ.) ይመሳሰላሉ፡፡

## 3.2.2. ዋና ዋና የእፅዋት ክፍሎች እና ተግባሮቻቸዉ



**ቁልፍ ቃል**

◆የእፅዋት ዋና ዋና ክፍሎች

### ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቁ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች

ዉድ ተማሪዎች!ይህንን ይዘት ተምራችሁ ካጠናቀቃችሁ በኋላ፡-

- ዋና ዋና የእፅዋት ክፍሎች እና ተግባራቸዉን ትዘረዝራላችሁ፡፡
- የስር፣ የግንድ ፣ የቅጠል እና የአበባ ጠቀሜታ ትገልጻላችሁ፡፡

### የእፅዋት ክፍሎች


**የተግባር ክንዋኔ 3.4: የግል ሥራ**

**ዓላማ፡-** የእፅዋት ክፍሎችን መዘርዘር፡፡

**መመሪያ፡-** ቀጥሎ ለቀረበዉ ጥያቄ መልስ ስጥ/ጭ፡፡

**ጥያቄ፡-**

1. ቀጥሎ በቀረበዉ ስዕል ላይ ከፊደል ሀ-መ የተመላከቱትን የእፅዋት ክፍሎችን ስም ተናገሪ/ር፡፡




ስዕል 3/3 የእፅዋት አካል ክፍሎች

የእፅዋት ክፍሎች ከመሬት በታች እና ከመሬት በላይ ተብለዉ በሁለት ይመደባሉ ፡፡ ከመሬት በታች ያለው የእፅዋት ክፍል ስር ይባላል፡፡ ከመሬት በላይ የሚገኙ የእፅዋት ክፍሎች የሚባሉት ደግሞ ግንድ፣ ቅርንጫፍ፣ ቅጠል እና አበባ ናቸው፡፡

## ሀ. ስር

### የተግባር ክንዋኔ 3.5: የቡድን ዉይይት

**ዓላማ፡-** የተክል ስር ለእፅዋት የሚሰጠዉን ጥቅም መለየት

- የስር ዓይነቶችን መለየት

**መመሪያ፡-** ስድስት አባላት ያሉት ቡድን መስርታችሁ ቀጥሎ ባሉት ጥያቄዎች ላይ በመወያየት መልስ አቅርቡ፡፡

**ጥያቄዎች፡-**

1. ስር ለእፅዋት የሚሰጠዉን ጥቅም ግለጹ፡፡
2. ከአካባቢያችሁ የተለያዩ የእፅዋት ዝሪያዎችን ወስዳችሁ የስሮቻቸዉን ልዩነት ግለጹ፡፡

የተክል ስር እፅዋቱን ከአፈር ጋር በማጣበቅ ውኃና የሚሙ ማዕድናትን ከአፈር ውስጥ በመውሰድ ለእፅዋቱ ላይኛው ክፍል ማስተላለፍ ነዉ፡፡ የእፅዋት ስሮች ሁለት ዓይነት ናቸዉ፡፡



ተራዘም ስሮች



ድራድር ስሮች

ስዕል 3/4 የስር ዓይነቶች

### ለ. ግንድ

**የተግባር ክንዋኔ 3.6: የቡድን ዉይይት**

**ዓላማ**፡- የግንድ ተግባርን መዘርዘር፡፡

- የግንድ ዓይነቶችን መለየት፡፡

**መመሪያ**፡- ስድስት አባላት ያሉት ቡድን መስርታችሁ ቀጥሎ ባሉት ጥያቄዎች ላይ በመወያየት መልስ አቅርቡ፡፡

**ጥያቄዎች**፡-

1. ግንድ ለእፅዋት የሚሰጠዉን ጥቅም ዘርዝሩ፡፡
2. በአካባቢያችሁ ያሉትን የእፅዋት ዝሪያዎች በመመልከት የግንዶቻቸዉን ልዩነት ግለጹ፡፡



**የእፅዋት ግንድ ዋና ዋና ተግባራት**

ግንድ ዉሃ እና የሟሙ ማዕድናትን ከሥርተቀብሎ
ለላይኞቹ የተክል ክፍሎች ሲያስተላልፍ ከቅጠሎ
ች ደግሞ የተዘጋጀ ምግብ በመቀበል ለሥር ያደር
ሳል፡፡ በተጨማሪ ግንድ የተክሉን ቅርንጫፎች፣
ቅጠሎች ፣ አበባዎችን እና ፍሬዎችን ይሸከማል፡፡

ሥዕል 3/5 የተክል ግንድ

## ሐ. ቅጠል

### የተግባር ክንዋኔ 3.7: የቡድን ዉይይት

ዓላማ :- የቅጠል ተግባርን መግለጽ፡፡


- የቅጠል ዓይነቶችን መግለጽ፡፡

መመሪያ:- ስድስት አባላት ያሉት ቡድን መስርታችሁ ቀጥሎ ባሉት ጥያቄዎች ላይ በመወያየት መልስ አቅርቡ፡፡

ጥያቄዎች:-

1. ቅጠል ለእፅዋት የሚሰጠዉን ጥቅም ዘርዝሩ፡፡
2. ከአካባቢያችሁ በርካታ የእፅዋት ዝሪያዎችን በማየት የቅጠሎቻቸዉን ልዩነት አብራሩ፡፡

የቅጠል ዋናው ተግባር ለተክሉ ምግብ ማዘጋጀት ነው፡፡



ስዕል3/6 የቅጠል ዓይነቶች

## መ. አበባ

**የተግባር ክንዋኔ 3.8: የጥንድ ዉይይት**

**ዓላማ**፡- አበባ ለእፅዋት የሚሰጠዉን ጥቅም መግለጽ፡፡


- የአበባ ዓይነቶችን መለየት፡፡

**መመሪያ**፡-ሁለት-ሁለት በመሆን ቀጥሎ ባሉት ጥያቄዎች ላይ በመወያየት ማብራሪያ አቅርቡ፡፡

ጥያቄዎች፡-

1. አበባ ለእፅዋት ምን ጥቅም ይሰጣል?
2. በአካባቢያችሁ ከሚገኙት እፅዋት ደማቅ አበባ ያላቸዉን ደማቅ አበባ ከሌላቸዉ ለይታችሁ አሳዩ፡፡

አበባ የእፅዋት መራቢያ ክፍል ነዉ፡፡ አንዳንድ እፅዋት ደማቅ አበባ ሲኖራቸዉ የሌሎቹ እፅዋት አበባ ደብዛዛ ነዉ፡፡



ደማቅ አበባዎች



ደብዛዛ አበባዎች

ስዕል 3/7 የአበባ ዓይነቶች

የአበባ ተግባር ለተክሉ ፍሬና ዘር ማፍራት፣ ለንቦች ምግብ የሚሆን ጣፋጭ ፈሳሽ ማዘጋጀት እንዲሁም ለቤትና ለአካባቢ ዉበት ይሰጣል፡፡

### መልመጃ 3.2

**መመሪያ፡-ቀጥሎ ለቀረቡት ጥያቄዎች ማብራሪያ ስጥ/ጭ፡፡**

1. የእ/ዋት ዋና ዋና ክፍሎችን ዘርዝሪ/ር፡፡
2. ከአፈር ማዕድንና ዉሃን በመዉሰድ ወደ ግንድ የሚያስተላልፈዉ

የእፅዋት ክፍል ምን ይባላል?

3. ግንድ ለተክሉ ምን አገልግሎት ይሰጣል?
4. ምግብ የሚያዘጋጀዉ የእፅዋት ክፍል ምን ይባላል?
5. የአበባ ተግባር ምንድን ነዉ?

## 3.2.3. ለእፅዋት እድገት አስፈላጊ የሆኑ ነገሮች



**ቁልፍ ቃላት**

- ዉኃ
- አየር
- አፈር
- የፀሀይ ብርሃን

### ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቅ አጥጋቢ የመማር ብቃት

ዉድ ተማሪዎች!ይህንን ይዘት ተምራችሁ ካጠናቀቃችሁ በኋላ፡-

- ለእፅዋት እድገት አስፈላጊ የሆኑ ነገሮችን ትዘረዝራላችሁ፡፡

**ለእፅዋት እድገት አስፈላጊ የሆኑ ዋና ዋና ነገሮች**

**የተግባር ክንዋኔ 3.9: የጥንድ ዉይይት**

**ዓላማ**፡-ለእፅዋት ዕድገት አስፈላጊ የሆኑ ነገሮችን መለየት፡፡

**መመሪያ**፡- ሁለት-ሁለት በመሆን ቀጥሎ ባለዉ ጥያቄ ላይ በመወያየት መልስ አቅርቡ፡፡

**ጥያቄ**፡-

1. ለዕፅዋት ዕድገት አስፈሊጊ የሆኑ ነገሮችን ለዩ፡፡

ለእፅዋት እድገት አስፈላጊ የሆኑ ዋና ዋና ነገሮች አፈር፣ ዉኃ፣ አየር እና የፀሃይ ብርሃን ናቸዉ፡፡

**ሙከራ 3/1 ለእፅዋት እድገት የሚያስፈልጉትን ነገሮች በሙከራ ማረጋገጥ**

## ሙከራውን ለመስራት የሚያስልጉ ነገሮች (ቁሳቁሶች)

- አራት በለም አፈር የተሞሉ ጣሳዎችን ማዘጋጀት
- አንድ ዓይነት የሆኑ ቅጠላማ ችግኞች ይኑራችሁ፣
- በጣሳዎቹ ላይ ከ1-4 ቁጥሮችን ጽፎ መለጠፍ፡፡

## የአሰራር ቅደም ተከተል

1. አራቱንም ችግኞች ለም አፈር ባለባቸዉ ጣሳዎች ውስጥ መትከል፡፡
2. አንድ ቁጥር የተፃፈበት ጣሳ ውስጥ የተተከለውን ችግኝ በፕላስቲክ ከረጢት ውስጥ በማድረግ አየር እንዳያገኝ ማድረግ
3. ሁለት ቁጥር የተፃፈበት ጣሳ ውስጥ የተተከለውን ችግኝ ውኃ እንዳያገኝ ማድረግ፡፡
4. ሶስት ቁጥር የተፃፈበት ጣሳ ውስጥ የተተከለውን ችግኝ የፀሐይ ብርሃን እንዳያገኝ ጨለማ ቦታ (ሣጥን ውስጥ) ማድረግ፡፡
5. አራት ቁጥር የተጻፈበት ጣሳ ዉስጥ የተተከለዉን ችግኝ ዉኃ ፣ አየር ፣ የፀሐይ ብርሃን እንዲያገኝ ማድረግ
6. ከአንድ ሣምንት በኋላ የአራቱንም ችግኞች እድገት በማየት ውጤቱን መመዝገብና ሪፖርት ማቅረብ፡፡

ዉድተማሪዎች!በሰራችሁት ሙከራ አፈር፣ ዉኃ፣ አየር እና የፀሃይ ብርሃን ለተክል እድገት አስፈላጊ መሆኑን ተገነዘባችሁ?

## መልመጃ 3.3

**መመሪያ፡ ከፍ ብሎ ከሰራችሁት ሙከራ ተነስታችሁ የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሽስ፡፡**

1. ለተክል እድገት አስፈላጊ ነገሮችን ጥቀሽ/ስ፡፡
2. ጥሩ እድገት እያሳየ ያለው ችግኝ በየትኛው ጣሳ ውስጥ ያለው ነው ? ለምን?
3. የጠወለገው (የደረቀው) ችግኝ በየትኛው ጣሳ ውስጥ ያለው ነው? ለምን?

4. ቅጠሎቹ ከአረንጓዴነት ወደ ቢጫነት የተቀየረዉ ችግኝ በየትኛው ጣሳ ውስጥ የተተከለው ነው? ለምን?

## 3.2.4. ኮምፖስት



ቁልፍ ቃል

◆ኮምፖስት

### ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቅ አጥጋቢ የመማር ብቃት

ዉድ ተማሪዎች!ይህንን ይዘት ተምራችሁ ካጠናቀቃችሁ በኋላ፡-

- ስለ ኮምፖስት ምንነት እና ጠቀሜታ ታብራራላችሁ፡፡

**የተግባር ክንዋኔ 3.10: የቡድን ዉይይት**

**ዓላማ**፡- የኮምፖስት ጥቅም መግለጽ

**መመሪያ**፡- ስድስት አባላት ያሉት ቡድን መስርታችሁ ቀጥሎ ባለዉ ጥያቄ ላይ በመወያየት መልስ አቅርቡ፡፡

**ጥያቄ**፡-

1. የኮምፖስት ጥቅም ምንድን ነዉ?

የአፈር ለምነትን ለማሻሻል ኮምፖስት መጨመር አስፈሊጊ ነው፡፡ ትርፍራፊ ምግቦችን እና የወዳደቁ (የረገፉ) ቅጠሎችን በመሰብሰብ ኮምፖስት አዘጋጅቶ መጠቀም እና የአፈር ለምነትን በመጨመር ለእፅዋት እድገት አጋዥ ሚና እንዲጫወት ማድረግ ይቻላል፡፡





ሀ. ኮምፖስት ሳይገባ በፊት




ለ. ኮምፖስት ከገባ በኋላ

ስዕል 3/8 ኮምፖስት ለአፈር ለምነት ይሰጣል

ዉድ ተማሪዎች! ኮምፖስት አዘጋጅታችሁ ለጓሮ አትክልት ልማት ማዋል ትችላላችሁ፡፡ ኮምፖስት የሚዘጋጀዉ የካርበንና የናይትሮጅን ምንጮችን በመጠቀም ነዉ፡፡




ስዕል 3/9 የኮምፖስት አዘገጃጀት

**ሙከራ 3/2 ኮምፖስት የአፈር ለምነትን በመጨመር ለእፅዋት እድገት አጋዥ መሆኑን በሙከራ ማረጋገጥ፡፡**

**ሙከራዉን ለመስራት የሚያስፈልጉ ነገሮች**

1. የተዘጋጀ ኮምፖስት
2. ችግኞች (ለምሳሌ:-ካሮት፣ሽንኩርት፣ ጎመን፣ የቡና ወይም የሌላ ዛፍ ችግኞችን ከአካባቢያችሁ መጠቀም ትችላላችሁ፡፡

**የአሰራር ቅደም ተከተል**

1. በትምህርት ቤት ግቢ ዉስጥ መደብ ለማዘጋጀት የሚሆን ቦታ አስፈቅዱ፡፡

2. የክፍሉ ተማሪዎች ለሶስት ወይም ለአራት ቡድን ሁኑ ::
3. በየቡድናችሁ ሁለት ሁለት የችግኝ መደቦችን አዘጋጁ::
4. በሁለቱም መደብ ላይ ተመሳሳይነት ያላቸዉን ችግኞች ትከሉ:: በሁለቱም መደብ ላይ ያሉት ችግኞች በአረም እንዳይበሉ ማረም እና መኮትኮት አለባችሁ::
5. በመቀጠል በአንደኛዉ መደብ ላይ ባሉት ችግኞች ዙሪያ ሁለት ወይም ሶስት ዙር ኮምፖስት ጨምሩበት:: በሁለተኛ መደብ ላይ አትጨምሩ::
6. በሁለቱ መደቦች ላይ ያሉትን ችግኞች ከ 3-4 ሳምንት ተከታትላችሁ ለዉጡን መዝግቡ::

## መልመጃ 3.4

**መመሪያ አንድ:-ቀደም ስል ከሰራችሁት ሙከራ ተነስታችሁ የሚከተለዉን ጥያቄ መልሽ/ስ::**

1. የትኛዉ ችግኝ የተሻለ እድገት አሳየ? ለምን?

## መልመጃ 3.5

**መመሪያ አንድ: ከሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች ዉስጥት ትክክል የሆነዉን "እዉነት" ትክክል ያልሆነዉን "ሐሰት" በማለት መልሽ/ስ**

1. ምግብ የሚዘጋጅበት የእፅዋት ክፍል ስር ይባላል::
2. አበባ የተክሉ መራቢያ አካል ነዉ::
3. ኮምፖስት የአፈር ለምነትን ይቀንሳል::
4. ሁሉም የእፅዋት ቅጠሎች ተመሳሳይ ቅርጽ አላቸዉ::
5. ስር በመሬት ዉስጥ የሚገኝ የተክል ክፍል ነዉ::

**መመሪያ ሁለት:-ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛዉን መልስ የያዘ ሆሄ ምረጭ/ጥ::**

1. ከሚከተሉት የተክል ክፍሎች ዉስጥ ዉሃ ከአፈር ዉስጥ የሚመጠዉ የትኛዉ ነዉ?

ሀ. አበባ　　　　ሐ. ቅርንጫፍ

ለ. ቅጠል　　　　መ. ስር

2. ለእፅዋት እድገት አስፈላጊ ያልሆነዉ የቱ ነዉ?

ሀ. ድንጋይ ለ. አየር ሐ. አፈር መ. ዉኃ

3. ቅጠልና ቅርንጫፎችን የሚሸከም የእፅዋት ክፍል የትኛዉ ነዉ?

ሀ. ስር ለ. አበባ ሐ. ግንድ መ. ፍሬ

## 3.3. በወረዳችን ዉስጥ የሚገኙ እንስሳት

### 3.3.1. እንስሳት



ቁልፍ ቃላት

◆ለማዳ እንስሳት ◆የዱር እንስሳት

ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቅ አጥጋቢ የመማር ብቃት

ዉድ ተማሪዎች!ይህንን ይዘት ተምራችሁ ካጠናቀቃችሁ በኋላ፡-

- የቤት እና የዱር እንስሳትን ትለያላችሁ፡፡

የንዑስ ርዕሱ ይዘት

- እንስሳት

**የተግባር ክንዋኔ 3.11: የቡድን ዉይይት**


**ዓላማ**፡- የቤት እና የዱር እንስሳትን መለየት

**መመሪያ**፡- ስድስት አባላት ያሉት ቡድን መስርታችሁ ቀጥሎ ባሉት ጥያቄዎች ላይ በመወያየት ማብራሪያ አቅርቡ፡፡

**ጥያቄዎች**፡-

1. የቤት እና የዱር እንስሳት ማለት ምን ማለት ነዉ?
2. በአካባቢያችሁ የሚገኙትን እንስሳት ስማቸዉን ዘርዝሩ፡፡
3. ከላይ ከዘረዘራችሁት እንስሳት መካከል የዱር እንስሳትን ለዩ፡፡

እንስሳት ከሰዎች ጋር በሚኖራቸዉ ቀረቤታ አንጻር የቤት (ለማዳ) እንስሳት እና የዱር እንስሳት ተብሎ በሁለት ይከፈላሉ።



ስዕል 3/10 የቤት እንስሳት በከፊል



ስዕል 3/11 የዱር እንስሳት በከፊል

## 3.3.2. የእንስሳት ጥቅም

ቁልፍ ቃል

◆ የእንስሳት ጥቅም

## ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቅ አጥጋቢ የመማር ብቃት

**ዉድ ተማሪዎች!ይህንን ይዘት ተምራችሁ ካጠናቀቃችሁ በኋላ፡-**

- የእንስሳትን ጥቅም ትዘረዝራላችሁ።

### የእንስሳት ጥቅም

**የተግባር ክንዋኔ 3.12: የጥንድ ዉይይት**


**ዓላማ**፡- የእንስሳትን ጥቅም መዘርዘር

**መመሪያ**፡- ሁለት-ሁለት በመሆን ቀጥሎ ባለዉ ጥያቄ ላይ በመወያየት ማብራሪያ አቅርቡ።


**ጥያቄዎች**፡-

1. እንስሳት ለሰዉ ልጆች የሚሰጡትን ጥቅም ዘርዝሩ።
2. ለመጓጓዣነት የሚያገለግሉ የቤት እንስሳት የትኞቹ ናቸዉ?

እንስሳት ለሰዉ ልጆች የተለይዩ ጥቅሞችን ይሰጣሉ ከእነርሱም መካከል ዋና ዋናዎቹ ለምግብነት፣ለማጓጓዣነትና ለቤት ጥበቃ አገልግሎት ናቸዉ።



ስዕል 3/12 ለምግብነት የሚዉሉ እንስሳት በከፊል



ስዕል 3/13 ለማጓጓዣነት የሚያገለግሉ የቤት እንስሳት በከፊል



ስዕል 3/14 ዉሻ ቤት የመጠበቅ አገልግሎት ይሰጣል

## 3.3.3. የእንስሳት ምደባ



ቁልፍ ቃል

- የእንስሳት ምደባ

ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቅ አጥጋቢ የመማር ብቃት

ዉድ ተማሪዎች!ይህንን ይዘት ተምራችሁ ካጠናቀቃችሁ በኋላ፡-

- እንስሳትን ትመድባላችሁ፡፡

## የንዑስ ርዕስ ይዘት

- የእንስሳት ምደባ

### የተግባር ክንዋኔ 3.13: የቡድን ዉይይት

**ዓላማ፡-** የእንስሳትን ምደባ መግለጽ

**መመሪያ፡-** ስድስት አባላት ያሉት ቡድን መስርታችሁ ቀጥሎ ባለዉ ጥያቄ ላይ በመወያየት መልስ ስጡ፡፡

**ጥያቄዎች፡-**

1. የእንስሳት ምደባ ማለት ምን ማለት ነዉ?
2. በእንስሳት ምደባ ስርዓት ከሚታወቁ የእንስሳት ክፍሎች ዋና ዋናዎቹን ዘርዝሩ፡፡

እንስሳት ምደባ ማለት በእንስሳት መካከል ያለዉን መሠረታዊ መመሳሰል መነሻ በማድረግ በዓይነት ዓይነታቸዉ የመመደብ እና ስያሜ የመስጠት ዘዴ ነዉ፡፡ እንስሳት በዉጫዊ ገጽታቸዉ መሠረት አሳዎች፣ እንቁራሪት አስተኔዎች ፣ ገበሎ አስተኔዎች ፣ አዕዋፍት እና አጥቢዎች ተብለዉ በአምስት ክፍሎች ይመደባሉ፡፡

### ሀ. አሳዎች

### የተግባር ክንዋኔ 3.14: የግል ሥራ


**ዓላማ፡-** የአሳዎችን መኖሪያ መግለጽ

**መመሪያ፡-** ቀጥሎ ለቀረበዉ ጥያቄ መልስ ስጥ_ጭ፡፡

**ጥያቄ፡-**

1. አሳዎች መኖሪያቸዉ የት ነዉ?

አሳዎች በዉሃ ዉስጥ ብቻ የሚኖሩ እና እንቁላል በመጣል የሚራቡ እንስሳት ናቸዉ፡፡ አሳዎች የሚተነፍሱት በስንጥብ (ጊል) ስለሆነ ከዉሃ ዉጭ መኖር አይችሉም፡፡ የአሳዎች ቆዳ በቅርፊት የተሸፈነ ነዉ፡፡



ቆረሶ



አምባዛ



ሻርክ

ስዕል 3/15 አሳዎች

## ለ.እንቁራሪት አስተኔዎች

**የተግባር ክንዋኔ 3.15: የግል ሥራ**

**ዓላማ**:- የእንቁራሪቶችን እና የጉርጦችን መኖሪያ ቦታ መግለጽ

**መመሪያ**:- ቀጥሎ ላለዉ ጥያቄ መልስ ስጥ/ጭ።

**ጥያቄ**:-

1. በአካባቢያችሁ እንቁራሪት እና ጉርጥ አሉ? ካሉ የት እንደሚኖሩ ግለጹ።

እንቁራሪት እና ጉርጥ በዉሃ ዉስጥና በመሬት ላይ መኖር የሚችሉ ሲሆኑ እንቁላላቸዉን ዉሃ ዉስጥ በመጣል የሚራቡና በቆዳቸዉ ላይ ምንም ዓይነት ተጨማሪ ሽፋን የሌላቸዉ ናቸዉ።



እንቁራሪት



ጉርጥ

ስዕል 3/16 እንቁራሪት አስተኔዎች

## ሐ.ገበሎ አስተኔዎች ( ተሳቢ እና ተራማጅ እንስሳት)

### የተግባር ክንዋኔ 3.16: የቡድን ዉይይት


**ዓላማ**፡- በደረት የሚሳቡትን እና በእግራቸዉ የሚራመዱ ገበሎ አስተኔዎች መለየት

**መመሪያ**፡- ስድስት አባላት ያሉት ቡድን መስርታችሁ ቀጥሎ ለቀረበዉ ጥያቄ ላይ በመወያየት መልስ አቅርቡ፡፡

**ጥያቄ**፡-

1. በአካባቢያችሁ ከሚገኙት ገበሎ አስተኔዎች በደረት የሚሳቡትንና በእግር የሚራመዱትን ለይታችሁ ተናገሩ፡፡

ገበሎ አስተኔዎች ቆዳቸዉ በቅርፊት የተሸፈነ ሲሆን የሚራቡት እንቁላል በመጣል ነዉ፡፡ ከገበሎ አስተኔዎች እባብ ፣ ዘንዶና የመሳሰሉት በደረታቸዉ የሚሳቡ ሲሆኑ እንደ እንሽላሊት፣ ኤሊና አዞ የመሳሰሉት ደግሞ በእግራቸዉ የሚራመዱ ናቸዉ፡፡



ኤሊ



እንሽላሊት



አዞ



እባብ

ስዕል 3/17 ገበሎ አስተኔዎች

## መ.አዕዋፍ (ወፎች)

### የተግባር ክንዋኔ 3.17: የቡድን ዉይይት

**ዓላማ**:-የአከባቢያቸዉን አዕዋፍ ስም መዘርዘር

**መመሪያ**:-ስድስት አባላት ያሉት ቡድን መስርታችሁ ቀጥሎ ባለዉ ጥያቄ ላይ በመወያየት መልስ አቅርቡ፡፡

**ጥያቄ**:-


1. በአካባቢያችሁ የሚገኙ አዕዋፍ ስም ተናገሩ፡፡

አዕዋፍ ቆዳቸዉ በላባ የተሸፈነ ሲሆን የእግራቸዉ ታችኛዉ ክፍል ላይ የሚገኘዉ ቆዳ ግን ቅርፊት ለበስ ነዉ፡፡ አዕዋፍ በአፋቸዉ አካባቢ ጠንካራ ምንቃር ሲኖራቸዉ በእግር ጣቶቻቸዉ ላይ ሹልና ጠንካራ ጥፍር አላቸዉ፡፡ አዕዋፍ የሚራቡት እንቁላል በመጣል ሲሆን አብዛኛዎቹ ለመብረር የሚያስችላቸዉ ክንፍ አላቸዉ፡፡



ዶሮ


ዳክዬ


እርግብ


ንስር


ጥንብ አንሳ


ሰጎን

ስዕል 3/18 አዕዋፍ

## ሠ. አጥቢዎች

**የተግባር ክንዋኔ 3.18: የቡድን ዉይይት**

**ዓላማ**:- አጥቢ እንስሳትን በስም መጥቀስ

አጥቢዎች ከሌሎች እንስሳት በምን እንደሚለዩ መግለጽ


**መመሪያ**:- ስድስት አባላት ያሉት ቡድን መስርታችሁ ቀጥሎ በቀረቡት ጥያቄዎች ላይ በመወያየት ዘገባ አቅርቡ፡፡


**ጥያቄዎች**:-

1. በአካባቢያችሁ የሚገኙ አጥቢ እንስሳትን ስም ጥቀሱ፡፡
2. አጥቢ እንስሳት ከሌሎች እንስሳት የሚለዩት በምንድን ነዉ?

አጥቢ እንስሳት ቆዳቸዉ በፀጉር የተሸፈነ ነዉ፡፡ አጥቢ እንስሳት ጡት የሚያጠቡ እና አምሳያቸዉን በመዉለድ የሚራቡ ናቸዉ፡፡


አይጥ


ላም


ዝሆን


የሌሊት ወፍ


አሳ ነባሪ

ስዕል 3/19 አጥቢ እንስሳት በከፊል

ዉድ ተማሪዎች! ዉጫዊ ገጽታቸዉን መሠረት በማድረግ በአምስት ክፍሎች እንስሳት መመደባቸዉን አይታችኋል፡፡ ይሁን እንጂከዉጫዊ ገጽታቸዉ ባሻገር እንስሳትን በአረባባቸዉ፣ በእንቅስቃሴያቸዉ፣ በመኖሪያ ቦታቸዉና በአመጋገባቸዉ መሠረት መመደብም ሆነ መለየት ይቻላል፡፡

### ሀ) በአረባብ

**የተግባር ክንዋኔ 3.19: የቡድን ዉይይት**


**ዓላማ**፡- እንቁላል የሚጥሉትን እና አምሳያቸዉን የሚወልዱ እንስሳትን መለየት

**መመሪያ**፡- ስድስት አባላት ያሉት ቡድን መስርታችሁ ቀጥሎ ባለዉ ጥያቄ ላይ በመወያየት መልስ አቅርቡ፡፡

**ጥያቄ**፡-

1. በአካባቢያችሁ ከሚገኙት እንስሳት እንቁላል በመጣል የሚራቡ አምሳያቸዉን በመዉለድ ከሚራቡት ለዩ፡፡

እንስሳት በአረባብ ዘዴያቸው በሁለት ይመደባሉ፡፡ እነሱም፡- እንቁላል የሚጥሉ እና መሰላቸውን የሚወልዱ ናቸው፡፡



ስዕል 3/20 እንቁላል በመጣል የሚራቡ እንስሳት በከፊል





ስዕል 3/21 አምሳያቸዉን በመዉለድ የሚራቡ እንስሳት በከፊል

**ለ.በእንቅስቃሴያቸው**

## የተግባር ክንዋኔ 3.20: የቡድን ዉይይት

**ዓላማ**:- እንስሳትን በእንቅስቃሴያቸዉ መመደብ

**መመሪያ**:- ስድስት አባላት ያሉት ቡድን መስርታችሁ ቀጥሎ ባለዉ ጥያቄ ላይ በመወያየት መልስ ስጡ።

**ጥያቄ**:-

1. በአካባቢያችሁ የሚገኙ ልዩ ልዩ እንስሳት ከቦታ ወደ ቦታ እንዴት እንደሚንቀሳቀሱ አብራሩ።

እንስሳት ከእንቅስቃሴያቸዉ አንጻር በሰማይ የሚበሩ፣ መሬት ለመሬት በደረታቸዉ የሚሳቡ፣ በእግራቸዉ የሚራመዱና በዉሃ ዉስጥ የሚዋኙ ተብለው ይመደባሉ።





ስዕል3/22 በእግራቸዉ የሚራመዱ እንስሳት በከፊል



ስዕል3/23 በሰማይ የሚበሩ እንስሳት በከፊል



ስዕል 3/24 መሬት ለመሬት በደረታቸዉ የሚሳቡ እንስሳት በከፊል



ስዕል 3/25 ከዉሃ ዉጪ መኖርና መንቀሳቀስ የማይችሉ እንስሳት በከፊል

## ሐ. በአመጋገባቸዉ

### የተግባር ክንዋኔ 3.21: የቡድን ዉይይት

**ዓላማ**:- በአመጋገባቸዉ እንስሳትን መመደብ

**መመሪያ**:- ስድስት አባላት ያሉት ቡድን መስርታችሁ ቀጥሎ ባለዉ ጥያቄ ላይ በመወያየት መልስ ስጡ፡፡

**ጥያቄ**:-

1. እንስሳት በአመጋገባቸዉ በስንት ይመደባሉ?

እንስሳት በአመጋገባቸዉ መሠረት በሶስት ይመደባሉ፡፡ እነርሱም:- እፅዋት በል፣ ስጋ በል እና እፅዋትና ስጋ በል ናቸዉ፡፡

እፅዋት በል እንስሳት፡-ሳር በመጋጥና ቅጠላቅጠል በመቀንጠስ የሚመገቡ እንስሳት ናቸዉ፡፡

**ለምሳሌ**:- በሬ፣በግ ፣ ቀጭኔ ፣ፌየል ፣ግመል፣የመሳሰሉት ናቸዉ፡፡



ስዕል 3/26 እፅዋት በል እንስሳት በከፊል

ስጋ በል እንስሳት፡ የሌሎች እንስሳትን ስጋ የሚመገቡ ናቸዉ፡፡ ለምሳሌ፡ አንበሳ ፣ ጅብ ፣ ዉሻ፣ ቀበሮ፣ አቦሸማኔ የመሳሰሉት ናቸዉ፡፡






ስዕል 3/27 ስጋ በል እንስሳት በከፊል

**እፅዋት እና ስጋ በል እንስሳት**:- እፅዋት እና ስጋ (ሁለቱንም ዓይነት) የሚመገቡ ናቸዉ።

**ለምሳሌ**:- ሰዉ፣ አይጥ፣ ዶሮ፣ ድብ፣ የመሳሰሉት ናቸዉ።





ስዕል 3/28 እፅዋት እና ስጋ በል እንስሳት በከፊል

**መ. መኖሪያ ቦታቸዉ**

## የተግባር ክንዋኔ 3.22: የቡድን ዉይይት


**ዓላማ**:- በመኖሪያ ቦታቸዉ እንስሳትን መመደብ

**መመሪያ**:- ስድስት አባላት ያሉት ቡድን መስርታችሁ ቀጥሎ ባለዉ ጥያቄ ላይ በመወያየት መልስ ስጡ።


**ጥያቄ**:-

1. በአካባቢያችሁ የሚገኙትን እንስሳት በውሃ ውስጥ የሚኖሩ፣በመሬት ላይ የሚኖሩ እና በውሃና በመሬት የሚኖሩ በማለት መድቡ።


እንስሳት በአኗኗራቸው ወይም በሚኖሩበት ቦታ መሰረት በመሬት ላይ የሚኖሩ፣ በውሃ ውስጥ የሚኖሩ እና በውሃና በመሬት የሚኖሩ ተብለው በሶስት ዋና ዋና ክፍሎች ይመደባሉ።



ስዕል 3/29 በውኃ ውስጥ የሚኖሩ እንስሳት በከፊል



ስዕል3/30 በመሬት ላይ የሚኖሩ እንስሳት በከፊል



ስዕል3/31 በመሬት እና በውሃ ውስጥ የሚኖሩ እንስሳት በከፊል

## መልመጃ 3.6

**መመሪያ አንድ:-ቀጥሎ ለቀረቡት ጥያቄዎች ትክክለኛዉን መልስ የያዘዉን ሆሄ ምረጥ/ጭ::**

ከሚከተሉት እንስሳት በዉሃ ዉስጥ ብቻ የሚኖረዉ የቱ ነዉ?

ሀ. ላም　　　　ሐ. አሳ

ለ. ወፍ　　　　መ. እባብ

3. በዉሃ ዉስጥ የሚኖር አጥቢ እንስሳ የትኛዉ ነዉ?

ሀ. አሳነባሪ　　　　ሐ. ዶሮ

ለ. በግ　　　　መ. ፍየል

4. ከሚከተሉት ዉስጥ እፅዋት በል ያልሆነዉ የቱ ነዉ?

ሀ.ፍየል　　　　ሐ. ነብር

ለ.ዝሆን　　　　መ. ቀጭኔ

5. ከሚከተሉት ዉስጥ ቆዳዉ በቅርፊት የተሸፈነ እንስሳ የትኛዉ ነዉ?

ሀ. እባብ　　　　ሐ. በሬ

ለ.ዶሮ　　　　መ. ዳክዬ

**መመሪያ ሁለት:-ቀጥሎ ለቀረቡት ጥያቄዎች መልስ ስጡ::**

1. አጥቢ እንስት ቆዳቸዉ የተሸፈነዉ በምንድን ነዉ?
2. አዕዋፍ ከሌሎች እንስሳት በምን በምን ይለያሉ?
3. ገበሎ አስተኔዎች ከእንቅስቃሴ አንጻር በስንት ይከፈላሉ?
4. ቀጥሎ በሳጥን ዉስጥ የተዘረዘሩትን እንስሳት እፅዋት በል፣ ሥጋ በል ወይም እፅዋትና ሥጋ በል በማለት ለዩ::

ላም ፣ አይጥ ፣ እባብ ፣ ጅብ ፣ ሰው ፣ ቀበሮ ፣ጥንብ አንሳ ፣አንበሳ፣ ግመል፣ ድብ፣ ዶሮ

## 3.4. በወረዳችን ዉስጥ የሚገኙ የተፈጥሮ ሐብቶች



### ቁልፍ ቃላት

- የተፈጥሮ ሀብት
- እንስሳት
- ብርቅዬ እንስሳት
- እፅዋት
- ዉኃ
- አፈር
- አየር
- ማዕድን

### ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቁ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች

ዉድ ተማሪዎች!ይህንን ይዘት ተምራችሁ ካጠናቀቃችሁ በኋላ፡-

- በአካባቢያችሁ የሚገኙ የተፈጥሮ ሀብቶችን ትዘረዝራላችሁ፡፡
- የተፈጥሮ ሀብቶችን ጥቅም ትገልጻላችሁ፡፡

### የንዑስ ርዕስ ይዘቶች

- የተፈጥሮ ሀብት
- የተፈጥሮ ሀብት ዓይነቶች

### 3.4.1. የተፈጥሮ ሀብት

**የተግባር ክንዋኔ 3.23: የቡድን ዉይይት**

**ዓላማ፡-** በአካባቢያችሁ የሚገኙትን የተፈጥሮ ሀብቶችን መለየት

**መመሪያ፡-** ስድስት አባላት ያሉት ቡድን መስርታችሁ ቀጥሎ ባሉት ጥያቄዎች ላይ በመወያየት መልስ አቅርቡ፡፡

**ጥያቄዎች፡-**

1. በአካባቢያችሁ የሚገኙትን የተፈጥሮ ሀብቶችን ዘርዝሩ፡፡ 2. ከዘረዘራችሁት የተፈጥሮ ሀብቶች በወረዳችሁ የሚገኙትን ለዩ፡፡

የተፈጥሮ ሀብቶች የሚባሉት ለሰው ልጅ መኖር አስፈላጊ የሆኑ በአካባቢያችን የሚገኙ ነገሮች ሲሆኑ ዋና ዋናዎቹ እፅዋት፣ እንስሳት ፣

ውሃ፣ አየር፣ አፈር፣ ማዕድናትና የነዳጅ ዘይት ናቸው፡፡

## 3.4.2. የተፈጥሮ ሀብት ዓይነቶች

### ሀ. እፅዋት

**የተግባር ክንዋኔ 3.24: የቡድን ዉይይት**

**ዓላማ**፡- የእፅዋት ዓይነቶችን መዘርዘር

- እፅዋት ከሚሰጡት አገልግሎት ረገድ መመደብ፡፡

**መመሪያ**፡-ቀጥሎ በቀረቡት ጥያቄዎች ላይ ተወያዩና መልስ አቅርቡ፡፡

**ጥያቄዎች**፡-

1. በአካባቢያችሁ የሚገኙትን የእፅዋት ዓይነቶች ዘርዝሩ፡፡
2. በአካባቢያችሁ የሚገኙትን የእፅዋት ጥቅሞችን ጻፉ፡፡

እፅዋት ለሰዉ ልጅ ምግብነት ፣ ለመጠለያ መስሪያ፣ ለመድሃኒትነት፣ ለልብስ መስሪያ፣ ወዘተ. የሚያገለግሉ የተፈጥሮ ሀብቶች ናቸዉ፡፡

ለሰው ልጅ ምግብነት የሚውሉ እፅዋት ለምሳሌ፡ እንሰት ፣ በቆሎ ፣ ስንዴ ፣ አተር፣ ድንች፣ ወዘተ.ናቸው፡፡

### ለ. እንስሳት

**የተግባር ክንዋኔ 3.25: የቡድን ዉይይት**

**ዓላማ**፡- የቤት እና የዱር እንስሳት ስም መዘርዘር

- የቤት እንስሳት ጥቅሞች ማብራራት

**መመሪያ**፡- ስድስት አባላት ያሉት ቡድን መስርታችሁ ቀጥሎ ባሉት ጥያቄዎች ላይ በመወያየት መልሱ፡፡

**ጥያቄዎች**፡-

1. በአካባቢያችሁ የሚገኙትን የቤትና የዱር እንስሳት ስም ዘርዝሩ፡፡
2. የቤት እንስሳት ለሰው ልጅ የሚሰጡትን ጥቅሞች አብራሩ፡፡

እንስሳት የዱርና የቤት በመባል በሁለት ይመደባሉ፡፡ የዱር እንስሳት የሚኖሩት በጫካ ዉስጥ ሲሆን የቤት እንስሳት ደግሞ ከሰው ጋር ተላምደው በቤት እና በቤት አካባቢ የሚኖሩ ናቸው፡፡

ብርቅዬ እንስሳት

**የተግባር ክንዋኔ 3.26: የጥንድ ዉይይት**


**ዓላማ**፡- ብርቅዬ እንስሳትን መጥቀስ


**መመሪያ**፡- በጥንድ በመሆን ቀጥሎ በቀረቡት ጥያቄዎች ላይ ተወያይታችሁ መልስ ስጡ፡፡

**ጥያቄዎች**፡-


1. በአካባቢያችሁ ብርቅዬ እንስሳት አሉ? ካሉ በስም ጥቀሱ፡፡
2. ብርቅዬ እንስሳት ከሌሎች የዱር እንስሳት በምን ይለያሉ?

በአንድ አገር ብቻ የሚገኙ የዱር እንስሳት ብርቅዬ እንስሳት ይባላሉ፡፡ ብርቅዬ እንስሳት የቱርስት መስህብ ስለሆኑ ለአገር ምጣኔ ሀብት እድገት አስተዋጽኦ አላቸዉ፡፡ ስለሆነም የተለየ ጥበቃ እና እንክብካቤ ያስፈልጋቸዋል፡፡


ዋልያ


ኒያላ


ጭላዳ ዝንጀሮ


ቀይ ቀበሮ

ስዕል 3/32 ከአገራችን ብርቅዬ የዱር እንስሳት በከፊል

### ሐ. ውኃ

**የተግባር ክንዋኔ 3.27: የቡድን ውይይት**

**ዓላማ**:- የዉኃን ምንነት መግለጽ

- ዉኃ ለምን እንደሚጠቅም ማብራራት

**መመሪያ**: ስድስት አባላት ያሉት ቡድን መስርታችሁ ቀጥሎ ባሉት ጥያቄዎች ላይ በመወያየት መልስ አቅርቡ።

**ጥያቄዎች**:-

1. ዉኃ ምንድን ነዉ?
2. ዉኃ ለምን እንደሚጠቅም አብራሩ?

ዉኃ ቀለም፣ ጣዕም እና ሽታ የሌለዉ ፈሳሽ ነገር ነዉ። አብዛኛዉ የመሬት ክፍል የተሸፈነዉ በዉኃ ነዉ። ዉኃ ሕይወት ላላቸዉ ነገሮች ሁሉ በጣም አስፈላጊ ነዉ። የሰዉ ልጅ ዉኃን ለመጠጥ፣ ምግብለማዘጋጀት፣ የግል ንጽህና ለመጠበቅ፣ ለመጓጓዣነት፣ የኤለክትሪክ ኃይል ለማመንጨት፣ ለአሳ እርባታና ለመስኖ ይጠቀምበታል።

### መ. አየር

**የተግባር ክንዋኔ 3.28: የጥንድ ውይይት**

**ዓላማ**:- ስለ አየር ምንነት መናገር ።

- የአየር አስፈላጊነትን መግለጽ።

**መመሪያ**:- በጥንድ ሆናችሁ ቀጥሎ በቀረቡት ጥያቄዎች ላይ በመወያየት መልስ አቅርቡ።

**ጥያቄዎች**:-

1. አየር ምንድን ነዉ?
2. እ ፅዋት እና እንስሳት ያለ አየር መኖር ይችላሉ? ለምን?

አየር የብዙ ጋሶች ድብልቅ ነዉ፡፡ አየር ሕይወት ላላቸዉ ነገሮች ሁሉ ያስፈልጋል፡፡ በተጨማሪ አየር የመኪና ፣ የሞተር ሣይክል፣ የብስክሌት ጎማ እና የተለያዩ ኳሶችን ለመሙላት ይጠቅማል፡፡

ሠ. አፈር

**የተግባር ክንዋኔ 3.29: የቡድን ዉይይት**

**ዓላማ**፡- የአፈርን ጠቀሜታ ማብራራት

**መመሪያ**፡- ቀጥሎ ባሉት ጥያቄዎች ላይ በመወያየት መልስ አቅርቡ፡፡

**ጥያቄዎች**፡-

1. አፈር ለምን ይጠቅማል?
2. አፈር ከምን ይፈጠራል? እንዴትስ ይፈጠራል?

አፈር ከድንጋይ ስብርባሪ፣ ከእንስሳት እና እፅዋት ቅሪተ አካል የተፈጠረ ነው፡፡ እንስሳት እና እፅዋት ሲሞቱ አካላቸው ይበሰብስና ወደ አፈርነት ይለወጣል፡፡ አፈር ለእፅዋት እድገት አስፈላጊ ከሆኑ ነገሮች አንዱ ነዉ፡፡ ሶስት ዋና ዋና የአፈር ዓይነቶች አሉ፡፡ እነርሱም፡- አሸዋማ፣ ሸክላማ እና ለም አፈር ናቸዉ፡፡

ረ. ማዕድን

**የተግባር ክንዋኔ 3.30: የቡድን ዉይይት**

**ዓላማ**፡- የማዕድናትን ጥቅም መዘርዘር

**መመሪያ**፡- ቀጥሎ ባለዉ ጥያቄ ላይ በመወያየት መልስ አቅርቡ፡፡

**ጥያቄ**፡-

1. ከማዕድን የሚሠሩ ጌጣጌጦች እና መገልገያ መሳሪያዎችን ዘርዝሩ፡፡

ማዕድን በመሬት ዉስጥ የሚገኝ የተፈጥሮ ሀብት ነዉ፡፡ ወርቅ፣ ብር፣ነሐስ ፣መዳብ፣ አልማዝ እናብረት የማዕድን ዓይነቶች ናቸዉ፡፡ ከማዕድናት ጌጣጌጥ እና ልዩ ልዩ መገልገያ መሳሪያዎች ይዘጋጃሉ፡፡

ሀብል፣ ቀለበት፣ አምባር እና አልቦ ከማዕድናት የሚሰሩ ጌጣጌጦች ሲሆኑ እንደ ገጀራ፣ ማጭድ፣ ቢላ፣ አካፋ የመሳሰሉት ደግሞ ከማዕድናት የሚሰሩ መገልገያ መሳሪያዎች ናቸዉ፡፡

መልመጃ 3.7

መመሪያ:-ቀጥሎ ለቀረቡት ጥያቄዎች መልስ ስጡ፡፡

1. ለሰው ልጅ መኖር አስፈላጊ የሆኑ ማናቸውም በተፈጥሮ አካባቢ የሚገኙ ነገሮች ምን ይባላሉ?
2. እንስሳት ለሰዉ ልጅ ከሚሰጣቸዉ ጥቅሞች ሦስቱን ጥቀሱ፡፡
3. ዉሃ ለሰዉ ልጅ ከሚሰጣቸዉ ጥቅሞች ዋና ዋናዎቹን ጻፉ፡፡
4. የአፈር ዓይነቶችን ዘርዝሩ፡፡
5. ማዕድናት ከየት ይገኛሉ?

## 3.5. አካባቢያችንን መንከባከብ

አካባቢያችን ማለት ህይወት ያላቸዉና ህይወት የሌላቸዉ ነገሮችን እንድሁም የተፈጥሮ እና ሰዉ ሰራሽ ነገሮችን አጠቃልሎ የያዘ አሃድ ነዉ ፡፡ ማንኛዉም የተፈጥሮ ሆነ ሰዉ ሰራሽ ሀብቶች ዘላቂ እና ለትዉልድ ተሻጋሪ ጠቀሜታ እንድሰጡ ከፈለግን ትኩረት እና እንክብካቤ ማድረግ ይገባናል፡፡ የአካባቢ እንክብካቤ ባጠቃላይ የተፈጥሮ ሀብት እና ሰዉ ሰራሽ ሀብት ጥበቃን ይመለከታል፡፡

### 3.5.1. በአካባቢያችን የሚገኙ የተፈጥሮ ሀብት እንክብካቤ



ቁልፍ ቃላት

- ሀብቶች
- ተፈጥሮአዊ ሀብት
- እንክብካቤ/ ጥበቃ

## ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቁ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች

ዉድ ተማሪዎች!ይህንን ይዘት ተምራችሁ ካጠናቀቃችሁ በኋላ፡-

- የተፈጥሮ ሀብቶችን ትለያላችሁ፡፡
- በአካባቢያችሁ የሚገኙትን የተፈጥሮ ሀብቶች ትንከባከባላችሁ፡፡
- የተፈጥሮ ሀብት እንክብካቤ መንገዶችን ትለያላችሁ፡፡

## የንዑስ ርዕስ ይዘቶች

- ሀብት
- የተፈጥሮ ሀብት እንክብካቤ በቤት እና በትምህርት ቤት ሀብት

### የተግባር ክንዋኔ 3.31: የቡድን ዉይይት

**ዓላማ**፡- የተፈጥሮ ሀብት እንክብካቤ አስፈላጊነት መግለጽ

- የተፈጥሮ በሀብቶች ላይ የተደቀኑ ችግሮችን ምን እንደሆኑ መለየት

**መመሪያ**፡- ቀጥሎ በቀረቡት ጥያቄዎች ላይ በመወያየት መልስ አቅርቡ፡፡

**ጥያቄዎች**፡-

1. የተፈጥሮ ሀብቶችን መንከባከብ ለምን አስፈለገ ?
2. በአካባቢያችሁ የተፈጥሮ ሀብቶች እና በሰዉ ሰራሽ ሀብቶች ላይ የተጋረጡ ችግሮች አሉ? ካሉ ምን ምን ናቸዉ፡፡

ማንኛዉም ለሰዉ ልጅ ጥቅም የሚዉሉ ተፈጥሮአዊና ሰዉ ሰራሽ ነገሮች በሙሉ ሀብት በመባል ይታወቃሉ፡፡ ዉሃ፣ አፈር ፣ አየር፣ ማዕድናት ፣ እጸዋት እና እንስሳት በተፈጥሮ የሚገኙ ሀብቶች ሲሆኑ የመንግስት ተቋማት ፣ ማህበራዊ ተቋማት፣ መካነ ቅርሶች ፣ የኃይል ማኖት ተቋማት፣ የመሳሰሉት ደግሞ ሰዉ ሰራሽ ሀብቶች ናቸዉ፡፡ ሀብቶችን መጠበቅ ማለት ለብክነት እና ለጉዳት ከሚዳርጉ ተግባራትመከላከል ማለት ነዉ፡፡ እነዚህን ሀብቶች ተገቢዉ ጥበቃና እንክብካቤሳናደርግለት በግድየለሽነት ከተጠቀምንባቸዉ ለጉዳት ይዳረጉ እና ሙሉ በሙሉ ሊጠፉ ይችላሉ፡

፡ ነገር ግን በጥንቃቄና በእንክብካቤይዘን ከተጠቀምንባቸዉ ዘላቂ እና አስተማማኝ አገልግሎት ይሰጡናል፡፡

## የተፈጥሮ ሀብት እንክብካቤ በቤት እና በትምህርት ቤት

### የተግባር ክንዋኔ 3.32: የቡድን ዉይይት

**ዓላማ**፡- የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃ እንዴት እንደሚካሄድ መግለጽ

- እንደገና ጥቅም ላይ የሚዉሉ እቃዎችን መለየት
- ተመልሶ ለፋብሪካ ግብዓት የሚሆኑ እቃዎችን መለየት

**መመሪያ**፡- ስድስት አባላት ያሉት ቡድን መስርታችሁ ቀጥሎ ባሉት ጥያቄዎች ላይ በመወያየት መልስ አቅርቡ፡፡

**ጥያቄዎች**፡-

1. የተፈጥሮ ሀብቶችን በቤታችሁ እና በትምህርት ቤታችሁ እንዴት ትጠብቃላችሁ?
2. እንደገና ጥቅም ላይ መዋል የሚችሉ እቃዎችን ዘርዝሩ፡፡
3. በአከባቢያችሁ ተመልሶ ለፋብሪካ ግብዓት በመሆን ሌላ እቃ ሊሠራባቸዉ የሚችሉ ቁሳቁሶችን ዘርዝሩ፡፡
4. ከዘንባባ ወይም ከቃጫ የተሰራ ዘምቢል ለዕቃ መያዣነት መጠቀም የፕላስቲክ ከረጢት ከመጠቀም የሚሻለዉ በምንድን ነዉ?

### ሀ. የተፈጥሮ ሀብት እንክብካቤ በቤት

አንዳንድ ቁሳቁሶችን ከቤታችን አዉጥተን በየቦታዉ ከምንጥላቸዉ ይልቅ የአገልግሎት ጊዜያቸዉን ማራዘም ወይም ለሌላ አገልግሎት እንደገና መጠቀም ያስፈልጋል፡፡ በሌላ መልኩ ለእኛ የማይጠቅሙ

አንዳንድ ቁሳቁሶችን ወደ ፋብሪካ መልሶ በመላክ ጥቅም ላይ ማዋልይቻላል፡፡ ይህንን በማድረግ የተፈጥሮ ሀብት ብክነትን እና የአካባቢ ብክለትን አስቀረን ማለት ነዉ፡፡




እንደገና ጥቅም መስጠት የሚችሉ ቁሳቁሶች በከፊል



ተመልሶ ለፋብሪካ ግብዓት መሆን የሚችሉ ቁሳቁሶች በከፊል

ስዕል 3/33 እንደገና ጥቅም ላይ የሚዉሉና ተመልሶ ለፋብሪካ ግብዓት የሚሆኑ ቁሳቁሶች

በአጠቃላይ ቆሻሻን ለመቆጣጠርና አካባቢን ከብክለት ለመታደግ የሚረዱ ሶስት ዋና ዋና መንገዶች አሉ፡፡ እነርሱም፡ መቀነስ፣ መጠቀም እና መመለስ ናቸዉ፡፡




ስዕል 3/34 አካባቢያችንን ከብክለት ለመታደግ የሚረዱ ሶስት መንገዶች

ከፍ ብሎ የተጠቀሱትን መንገዶች ከመተግበር ጎን ለጎን በቤታች የተፈጥሮ ጥበቃ ለማድረግ የጓሮ አትክልቶችንና ችግኞችን መትከልና መንከባከብ ፣ እርከን በመሥራት የአፈር መሸርሸርን መከላከል ይኖርብናል:: አንዳንድ የአገለግሎት ጊዜያቸዉን የጨረሱ ዕቃዎችን የተለያየ ባህላዊ

ዘዴዎችን በመጠቀም አዳድስ እና ለቤት ዉስጥ አገለግሎት የሚዉሉ ዕቃዎችን በመስራት መጠቀም ስቻል በሌላ በኩል የአከባቢ ንፅህና ለመጠበቅ ጉልህ አስተዋጽኦ እናበረክታለን ፡፡

**ለምሳሌ፡-** ያረጁ የዕቃ ማሰሪያ ፕላስትክ ገመዶችን በመጠቀም ዘንቢል መስራት ይቻላል

- ያረጁ የማዳበሪያ ኬሻዎችን በመጠቀም የእንስሳት ማሰሪያ ገመድ መስራት ይቻላል
- ያረጁ የዉሃ ባልዲዎችን በመጠቀም አበባ መትከል

**ለ. የተፈጥሮ ጥበቃ በትምህርት ቤት**

በትምህርት ቤት ውስጥ ለተፈጥሮ ጥበቃ ከምናደርግባቸው ዜዴዎች ውስጥ ጥቂቶቹ፡ ቆሻሻን በየቦታዉ አለመጣል፣ የተጣለውን ቆሻሻ ሰብስቦ በጥንቃቄ ማስወገድ፣ በገላጣ ቦታዎች ችግኞችን በመትከል አፈር እንዳይሸረሸር ማድረግ ተጠቃሾች ናቸው፡፡

## 3.5.2. በአካባቢያችን የሚገኙ ሰዉ ሰራሽ ሀብት እንክብካቤ



**ቁልፍ ቃላት**

- ሰዉ ሰራሽ ሀብት
- እንክብካቤ/ ጥበቃ

**ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቁ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች**

ዉድ ተማሪዎች!ይህንን ይዘት ተምራችሁ ካጠናቀቃችሁ በኋላ፡

- በአካባቢያችሁ የሚገኙትን ሰዉ ሰራሽ ሀብቶች ትዘረዝራላችሁ፡
- የሰዉ ሰራሽ ሀብት ጠቀሜታ ታብራራላችሁ፡፡

### የንዑስ ርዕስ ይዘት

**በወረዳችን ዉስጥ የሚገኙ ሰዉ ሰራሽ ሀብቶች**

ሀ. የልማት ተቋማት

ለ. የኃይማኖት ተቋማት

ሐ. ማህበራዊ እና ባህላዊ ተቋማት

**በአካባቢያችን ዉስጥ የሚገኙ ሰዉ ሰራሽ ሀብቶች**

### የተግባር ክንዋኔ 3.33: የቡድን ዉይይት

**ዓላማ**:- የተ`ነ`ማት ዓይነቶችን መዘርዘር።

- የልዩ ልዩ ተ`ነ`ማትን አገልግሎት ማብራራት።

**መመሪያ**:- ስድስት አባላት ያሉት ቡድን መስርታችሁ ቀጥሎ ባሉት ጥያቄዎች ላይ በመወያየት መልስ አቅርቡ።

**ጥያቄዎች**:-

1. በአካባቢያችሁ ዉስጥ ምን ምን ዓይነት ተቋማት ይገኛሉ?
2. ከላይ የጠቀሳችኋቸዉተቋማትየሚሰጡትን አገልግሎት አብራሩ።

በወረዳችን ዉስጥ የሚገኙ ሰዉ ሰራሽ ሀብቶች የሚባሉት የሰዉ ልጆች አብሮ ለመኖር፣ ለመግባባት ፣ለመረዳዳት፣ ችግሮቻቸዉን ለመፍታትና ኑሮአቸዉን ለማሻሻል ሲሉ የገነቡት ተቋማት ናቸዉ።

እነርሱም፡-የልማት ተቋማት፣ ማህበራዊ ተቋማት፣ የኃይማኖት ተቋማት ባህላዊ ተቋማት፣ የመሳሰሉት ናቸው።

**ሀ.የልማት ተቋማት**:-

### የተግባር ክንዋኔ 3.34: የግል ሥራ

**ዓላማ**:- በአካባቢ የሚገኙ የልማት ተቋማትን መዘርዘር

**መመሪያ**:- ቀጥሎ ለቀረበዉ ጥያቄ መልስ ስጡ

**ጥያቄ**:-

1. በአካባቢያችሁ የሚገኙ የልማት ተቋማትን ስም ዘርዝሩ።

የልማት ተቋማት የሚባሉት የግብርና፣የገንዘብ፣የግንባታ፣ የኤሌክትሪክ ሀይል እና ሌሎች መሥሪያ ቤቶች ናቸው።




ባንክ ቤት



ከፍተኛ ምርት የሚሰጡ የቀንድ ከብቶች ማራቢያ ማዕከል

ስዕል3/35 የልማት ተቋማት በከፊል

## ለ. የኃይማኖት ተቋማት

**የተግባር ክንዋኔ 3.35: የግል ሥራ**


**ዓላማ**:- በአካባቢ የሚገኙ የኃይማኖት ተ|ማትን መዘርዘር።

**መመሪያ**:- ቀጥሎ ለቀረበዉ ጥያቄ መልስ ስጡ።

**ጥያቄ**:-

1. በአካባቢያችሁ የሚገኙ የኃይማኖት ተቋማትን ዘርዝሩ።

የኃይማኖት ተቋማት ሰዎች የእምነት አገልግሎቶችን የሚያገኙበት እና ግብረገብ ትምህርት የሚማሩበት ነዉ። ቤተክርስቲያን እና መስጅድ ኃይማኖታዊ ተቋማት ይባላሉ።



ስዕል 3/36 ኃይማኖታዊ ተቋማት

## ሐ. ማህበራዊ እና ባህላዊ ተቋማት

ባህላዊ ተቋማት የሚባሉት አንድ ማህበረሰብ ግጭትን ለመፍታት፣ ለመረዳዳት እና ለሌሎች ማህበራዊ ጉዳዮች የሚጠቀሙ ናቸዉ፡፡ ለምሳሌ ሽምግልና የተጣሉ ሰዎችን ለማስታረቅ ይረዳል፡፡ እቁብ ገንዘብ ለመቆጠብ ይጠቅማል፡፡



ስዕል 3/37 ማህበራዊና ባህላዊ ተቋም /ባህላዊ ሽምግልና

### መልመጃ 3.8

*መመሪያ- ቀጥሎ ለቀረቡት ጥያቄዎች መልስ ስጥ/ጭ፡፡*

1. በአካባቢያችሁ የሚገኙትን የልማት ተቋማት ስማቸዉን ዘርዝሩ፡፡
2. ሽምግልና ማህበራዊ ተቋም ነዉ፡፡ ጥቅሙን ግለጹ፡፡
3. ሀብቶችን መንከባከብ ያስፈለገዉ ለምንድን ነዉ?

## ማጠቃለያ

- የአየር ሁኔታ በአንድ አካባቢ ላይ የሚታይ የዕለቱ (የ24 ሰዓት) የአየር ፀባይ ነዉ፡፡
- የአየር ንብረት ማለት ደግሞ የአንድ አካባቢ የረጅም ጊዜ አማካይ የአየር ሁኔታ ማለት ነዉ፡፡
- የአየር ንብረት ለዉጥ በሰዉ ልጅ ሕይወት እና ኑሮ ላይ አዳዲስ ችግሮችን በማስከተል ላይ ይገኛል፡፡
- የተፈጥሮ ሀብቶች በተፈጥሮ የሚገኙና ለሰው ልጆች ጥቅም የሚሰጡ ናቸዉ፡፡ የተፈጥሮ ሀብቶች ውሃን ፣ አፈርን፣እፅዋ ትን፣ ማዕድናትን፣አየርንና እንስሳትን ያካትታሉ፡፡
- እፅዋት ሕይወት ያላቸው ነገሮች ናቸው፡፡ ተክሎች የተለያዩ ክፍሎች አሏቸው፡፡እነሱም ቅጠል፣ ግንድ፣ሥርና አበባ ናቸው፡፡ እነዚህ የተክል ክፍሎች የተለያዩ ተግባራትን ያከናውናሉ፡፡እፅዋ ት ለእድገት የተለያዩ ነገሮች ያስፈልጓቸዋል፡፡ እነሱም አፈር፣ አየር፣ውሃና የፀሐይ ብርሃን ናቸው፡፡
- በአካባቢያችን የሚገኙትን ልዩ ልዩ እንስሳት በዉጫዊ ገጽ ታቸዉ፣ በአረባባቸው፣ በእንቅስቃሴያቸው፣በመኖሪያ ቦታ፣ ወዘተ.መለየትና መመደብ ይቻላል፡፡እንስሳት ለሰው ልጅ ልዩ ልዩ ጥቅም ይሰጣሉ፡፡ ለምሳሌ ለምግብነት፣ ለልብስና የጉል በት ሥራ ለመስራት ያገለግላሉ፡፡ ስለዚህ እንስሳትን በእንክብ ካቤ መያዝ ይገባናል፡፡

## የምዕራፉ ማጠቃለያ ጥያቄዎች

**መመሪያ አንድ፡- ከሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች ዉስጥ ትክክል ትክክል የሆነዉን "እዉነት" ትክክል ያልሆነዉን "ሐሰት" በማለት መልስ/ሽ፡፡**

1. እንቁራሪት የሚኖረዉ በዉሃ ዉስጥ ብቻ ነዉ፡፡
2. በእፅዋት ቅጠሎች መካከል ምንም ዓይነት ልዩነት የለም፡፡
3. የአየር ሁኔታ እና የአየር ንብረት አንድ ናቸዉ፡፡
4. እፅዋት ምግባቸዉን የሚያዘጋጁት በአበባቸዉ ነዉ፡፡
5. የአጥቢ እንስሳት ቆዳ በፅጉር የተሸፈነ ነዉ፡፡
6. የዛፍ ችግኞችን መትከልና መንከባከብ የአፈር መሸርሸርን ለመከላከል ይረዳል፡፡

**መመሪያ ሁለት፡-ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛዉን መልስ የያዘዉን ሆሄ ምረጭ/ጥ፡፡**

1. ከሚከተሉት ዉስጥ የተፈጥሮ ሐብት የሆነዉ የቱ ነዉ?
   - ሀ. ደን
   - ለ. ት/ቤት
   - ሐ. ክሊኒክ
   - መ. ቤተክርስቲያን
2. ከመሬት በታች የሚገኘዉ የእፅዋት ክፍል የትኛዉ ነዉ?
   - ሀ. አበባ
   - ለ.ስር
   - ሐ. ግንድ
   - መ. ቅጠል
3. ከሚከተሉት ዉስጥ ከእንስሳት የማናገኘዉ ጥቅም የቱ ነዉ?
   - ሀ. ምግብ
   - ለ.መጠለያ
   - ሐ. መጓጓዣ
   - መ. ልብስ
4. ከሚከተሉት እንስሳት አፅዋፍ ዉስጥ የማይመደበዉ የቱ ነዉ?
   - ሀ. ዶሮ
   - ለ. ሰጎን
   - ሐ. ንስር
   - መ. የሌሊት ወፍ
5. ከሚከተሉት ዉስጥ የአገራችን ብርቅዬ እንስሳ የቱ ነዉ?
   - ሀ. በሬ
   - ለ. ዋልያ
   - ሐ. ዝሆን
   - መ. ዝንጀሮ

6. ከሚከተሉት እንስሳት ዉስጥ እፅዋት በል የሆነው የቱ ነዉ?
   ሀ. ቀጭኔ ለ. አቦሸማኔ ሐ. አይጥ መ. አንበሳ
7. ከሚከተሉት ዉስጥ የስር ተግባር የሆነዉ የቱ ነዉ?
   ሀ. ተክሉን ከአፈር ጋር ማያያዝ
   ለ. ፊሬ ማፊራት
   ሐ. ለእፅዋቱ ምግብ ማዘጋጀት
   መ. የተክሉን አበባና ቅርንጫፍ መሸከም
8. ዘር እና ፍሬ የሚያፈራ የተክል ክፍል የቱ ነዉ?
   ሀ. ስር ለ.ግንድ ሐ. አበባ መ.ቅጠል
9. ከሚከተሉት እንስሳት ቆዳዉ በቅርፊት ያልተሸፈነዉ የቱ ነዉ?
   ሀ. አሳ ሐ. አዞ
   ለ.እንቁራሪት መ. እባብ
10. ለቤት ቁሳቁስ እና ጌጣጌጥ መስሪያነት የሚያገለግል የተፈጥሮ ሀብት የቱ ነዉ?
   ሀ. አየር ሐ.ዉሃ
   ለ. አፈር መ. ማዕድን

**መመሪያ ሦስት፡-ቀጥሎ በሰንጠረዥ ዉስጥ ከተራ ቁጥር 1 እስከ 4 የቀረቡትን ተቋማት ከሚሰጡት ጥቅም ጋር አዛምድ/ጅ፡፡**

| የተቋም ስም | የተቋሙ ጥቅም |
|---|---|
| | ሀ. ለመማር ማስተማር |
| ____1. የእንስሳት ማራቢያ ማዕከል | ለ. ፈጣሪን ለማመስገን |
| ____2. ትምህርት ቤት | ሐ. ያዘነን ለማፅናናት |
| ____3. መስጅድ | መ. የተጣለን ለማስታረቅ |
| ____4. እድር | ሠ. ምርጥ የእንስሳት ዘርን ማሰራጨት |

,

# ምዕራፍ አራት

# ማህበራዊ አካባቢያችን

## ከምዕራፉ የሚጠበቁ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች

ተማሪዎች የዚህን ምዕራፍ ይዘቶች ተምራችሁ ካጠናቀቃችሁ በኋላ:-

- የቤተሰብ አባላት እና ፍላጎቶቻቸውን ታብራራላችሁ።
- የቤተሰብን የጤና አጠባበቅ ፋይዳ ታስረዳላችሁ።
- የግል ንጽህና አጠባበቅ (የእጅ መታጠብ ፣የጥርስ መቦረሽ፣ወዘተ.) አስፈላጊነትን ትገልጻላችሁ።
- የት/ቤቱን እና የአካባቢዉን ማህበረሰብ አባላት ትለያላችሁ።
- በትምህርት ቤት በመሰረታችሁት አቻ ግንኙነት ልዩ ልዩ እንቅስቃሴዎችን ታከናዉናላችሁ።
- የትምህርት ቤቱን ደንቦች እና ሕጎች ታከብራላችሁ።

## በምዕራፉ የተካተቱ ይዘቶች

4.1 የቤተሰብ አባላት እና ፍላጎቶቻቸው

4.2 በትምህርት ቤት የተማሪዎች አቻ ግንኙነት እና ተግባራት

4.3 የግል እና የአከባቢ ንጽህና አጠባበቅ

**መግቢያ**

ዉድ ተማሪዎች! በአንደኛ ክፍል የአካባቢ ትምህርት ስለ ቤተሰብ አባላት እና ሚናዎቻቸዉን ተምራችኋል፡፡ በዚህኛዉ ምዕራፍ ደግሞስለ ቤተሰብ አባላት እና ፍላጎቶቻቸው፣በትምህርት ቤት የተማሪዎችአቻ ግንኙነትና ተግባራት እንዲሁም ስለ ግል እና አካባቢ ንጽህና አጠባበቅ ትማራላችሁ::

## 4.1. የቤተሰብ አባላት እና ፍላጎቶቻቸው

### 4.1.1. የቤተሰብ አባላት መሠረታዊ ፍላጎት



**ቁልፍ ቃላት**

◆ቤተሰብ ◆መሠረታዊ ፍላጎት

◆የቤተሰብ አባላት

**ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቅ አጥጋቢ የመማር ብቃት**

ዉድ ተማሪዎች!ይህንን ይዘት ተምራችሁ ካጠናቀቃችሁ በኋላ፡-

- የቤተሰብን አባላት ትለያላችሁ::
- የቤተሰብ አባላትን መሠረታዊ ፍላጎት ትጠቅሳላችሁ::

**የንዑስ ርዕስ ይዘቶች**

- የቤተሰብ አባላት
- የቤተሰብ አባላት መሠረታዊ ፍላጎት

**ሀ. የቤተሰብ አባላት**

**የተግባር ክንዋኔ 4.1: የቡድን ዉይይት**

**ዓላማ**፡-የቤተሰብ አባላትን መለየት

**መመሪያ**፡- ስድስት አባላት ያሉት ቡድን መስርታችሁ ቀጥሎ ባለዉ ጥያቄ ላይ በመወያየት መልስ አቅርቡ፡፡

**ጥያቄ**፡-

1. ዉድ ተማሪዎች! የእናንተን ቤተሰብ አባላት ዘርዝሩ፡፡

የቤተሰብ አባላት ማለት በአንድ ቤት ዉስጥ የሚኖሩ ሰዎች ናቸዉ:: እነሱምአባት፣ እናት፣ ወንድም እና እህት ናቸዉ፡፡ በተጨማሪም አያ፣ አጎት ፣ አክስት፣ እና ሌሎች በአንድ ቤት ዉስጥ አብሮ የሚኖሩ ሰዎችን ያጠቃልላል፡፡



ስዕል 4/1 የቤተሰብ አባላት

### ለ. የቤተሰብ አባላት መሠረታዊ ፍላጎት

**የተግባር ክንዋኔ 4.2: የቡድን ዉይይት**

**ዓላማ**፡- የቤተሰብ አባላት መሠረታዊ ፍላጎቶችን መዘርዘር

**መመሪያ**፡- ስድስት አባላት ያሉት ቡድን መስርታችሁ ቀጥሎ ባለዉ ጥያቄ ላይ በመወያየት መልስ አቅርቡ፡፡

**ጥያቄ**፡-

1. የቤተሰብ አባላት መሠረታዊ ፍላጎቶችን ዘርዝሩ

የአንድ ቤተሰብ መሠረታዊ ፍላጎት የሚባሉት ምግብ፣መጠለያ እና ልብስ ናቸዉ።

## 4.1.2.የቤተሰብ የጤና አጠባበቅ ፋይዳዎች (ጥቅሞች)



### ቁልፍ ቃላት

- ጤና
- የአካል ብቃት እንቅስቃሴ
- እረፍት
- የትምህርት ቤት ማህበረሰብ
- የትምህርት ቤት አካባቢ ማህበረሰብ
- የትምህርት ቤት ማህበረሰብ እና የትምህርት ቤት አካባቢ ማህበረሰብ ፍላጎት

### ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቅ አጥጋቢ የመማር ብቃት

ዉድ ተማሪዎች!ይህንን ይዘት ተምራችሁ ካጠናቀቃችሁ በኂላ፡-

- የጤና አጠባበቅ ጠቀሜታ ታብራራላችሁ።
- የትምህርት ቤት እና የትምህርት ቤት አካባቢ ማህበረሰብ ትለያላችሁ።
- የትምህርት ቤት ማህበረሰብ እና የትምህርት ቤት አካባቢ ማህበረሰብ ፍላጎት ትዘረዝራላችሁ።

### የንዑስ ርዕስ ይዘቶች

- የቤተሰብ የጤና አጠባበቅ ፋይዳዎች (ጥቅሞች)
- የትምህርትቤት ማህበረሰብ እና የአካባቢ ማህበረሰብ ፍላጎት

## የቤተሰብ የጤና አጠባበቅ ፋይዳዎች (ጥቅሞች)

### የተግባር ክንዋኔ 4.3: የቡድን ዉይይት

**ዓላማ፡-** ለጤናማ ሕይወት አስፈላጊ ነገሮችን መዘርዘር

- የአንድ ሰዉ ጤና መጓደል በቤተሰብ ላይ የሚያሳድረዉን ተጽእኖ መግለጽ

**መመሪያ፡-** ስድስት አባላት ያሉት ቡድን መስርታችሁ ቀጥሎ ባሉት ጥያቄዎች ላይ በመወያየት መልስ አቅርቡ፡፡

**ጥያቄዎች፡-**

1. ጤናማ ለመሆን ምን ያስፈልጋል?
2. ከቤተሰብ ዉስጥ የአንዱ ሰዉጤና መጓደል ምን ችግር ያመጣል?

ጤንነት ማለት የአንድ ሰዉ አካላዊ፣ አዕምሮአዊ እና ማህበራዊ ደህንነት ማለት ነዉ፡፡ ጤና ከቤተሰብ ኑሮ ጋር ቀጥተኛ የሆነ ግንኙነት አለዉ:: ሰዎች ጤነኛ እና ደስተኛ እንዲሆኑ የተመጣጠነ ምግብ፣ ንጹህ ዉሃ ፣ ንጹህ አየር እና ንጽህናዉ የተጠበቀ ልብስና መጠለያ ማግኘት ይኖርባቸዋል፡፡ በተጨማሪም የጤና አገልግሎት ፣በቂ እረፍት፣የአካል ብቃት እንቅስቃሴና መዝናኛ ያስፈልጋቸዋል፡፡

## የአካል ብቃት እንቅስቃሴ

### የተግባር ክንዋኔ 4.4: የጥንድ ዉይይት

**ዓላማ፡-** የአካል ብቃት እንቅስቃሴ ጥቅሞችን መግለጽ

- የአካል ብቃት እንቅስቃሴ ዓይነቶችን መዘርዘር

**መመሪያ፡-** ጥንድ በመሆን ቀጥሎ ባሉት ጥያቄዎች ላይ በመወያየት መልስ አቅርቡ፡፡

**ጥያቄዎች፡-**

1. የአካል ብቃት እንቅስቃሴ ማድረግ ለምን ይጠቅማል?
2. የአካል ብቃት እንቅስቃሴ ዓይነቶችን ዘርዝሩ፡፡

የአካል ብቃት እንቅስቃሴ መስራት ለጤንነትአስፈላጊ ነዉ፡፡ የአካልብቃት እንቅስቃሴ ለተስተካከለ ተክለ ሰዉነት፣ ለጥንካሬ እና ንቁ ለመሆን ይረዳል፡፡ የእግር ጉዞ፣ ብስክሌት ማሽከርከር፣ገመድ ዝላይ ፣የተለያዩ ስፖርታዊ እንቅስቃሴዎች ፣ ወዘተ.የአካል ብቃት እንቅስቃሴ ዓይነቶች ናቸዉ፡፡




ስዕል 4/2 የአካል ብቃት እንቅስቃሴ በከፊል

## እረፍት

**የተግባር ክንዋኔ 4.5: የግል ሥራ**

**ዓላማ**፡- የእረፍትን ትርጉም መናገር፡፡

- የእረፍትን አስፈላጊነት መግለጽ፡፡

**መመሪያ**፡- ቀጥሎ የቀረቡትን ጥያቄዎች ካነበባችሁ በº‌ላ መልሱ፡፡

**ጥያቄዎች፡-**

1. እረፍት ማለት ምን ማለት ነዉ?
2. እረፍት ለምን ያስፈልጋል?
3. የእረፍት እጦት የሚያስከትላቸዉን ችግሮች አብራሩ፡፡

እረፍት ማለት ማንኛዉም ሰዉ የተወሰነ ስራ ከፈጸመ በኋላ የተለያዩ ድርጊቶችን (እንቅልፍ መተኛት፣ ራዲዮ ማዳመጥ፣ ተሌቪዥን ማየት፣ መጻፍት ወይም ጋዜጦችን ማንበብ፣ ወዘተ.) በመፈጸም የሚጠቀምበት ጊዜ ማለት ነዉ፡፡ እረፍት የደከመ አዕምሮን እና የሰዉነት ክፍሎችን ለማደስ ይጠቅማል፡፡በቂ እረፍት የማይወስዱ ሰዎች ለድካም፣ ለሥራፍላጎት ማነስ፣ ለተለያዩ በሽታዎች፣ ለብስጭት፣ወዘተ..ይጋለጣሉ፡፡

## 4.1.3.የትምህርት ቤት ማህበረሰብ እና የአካባቢ ማህበረሰብ ፍላጎት

**የተግባር ክንዋኔ 4.6: የቡድን ዉይይት**

**ዓላማ**፡- የትምህርት ቤት ማህበረሰብ አባላት መዘርዘር፡፡

- የትምህርት ቤት ማህበረሰብ አባላትን ተግባር መናገር፡፡

**መመሪያ**፡- ቀጥሎ ባሉት ጥያቄዎች ላይ ተወያይታችሁ መልስ አቅርቡ፡፡

**ጥያቄዎች**፡-

1. የትምህርት ቤታችሁን ማህበረሰብ አባላት ዘርዝሩ፡፡
2. የትምህርት ቤት ማህበረሰብ አባላት ተግባራትን ተናገሩ፡፡

### የትምህርት ቤት ማህበረሰብ እና የአካባቢ ማህበረሰብ

የትምህርት ቤት ማህበረሰብ የሚባሉት በትምህርት ቤቱ ዉስጥ በቀጥታ የሚያገለግሉ(መምህራን፣ ርዕሰ መምህራን፣ ጥበቃ አባላት፣ ጽዳት ሰራተኞች ፣ ወዘተ.) እና የሚገለገሉ (ተማሪዎች) ናቸዉ፡፡

የትምህርት ቤት አካባቢ ማህበረሰብ የምንላቸዉ በትምህርት ቤቱ ዙሪያ የሚኖሩ፣ ከትምህርት ቤቱ አገልግሎት የሚያገኙና አገልግሎት የሚሰጡ ግለሰቦች፣ ድርጅቶች፣ ተ\ማት ወዘተ.ያጠቃልላል፡፡

## የትምህርት ቤት ማህበረሰብ እና የአካባቢ ማህበረሰብ ፍላጎት

ንጹህ የትምህርት ቤት አካባቢ፣ ምቹ የመማሪያ ክፍሎች፣ ጤናማ ተግባቦት፣ ቀልጣፋ አገልግሎት፣ የተሟላ የቁሳቁስ አቅርቦት፣ የንጹህ ዉሃ አቅርቦት፣ የስፖርት ማዘወተሪያ ቦታዎች፣ ቤተ መጽሀፍት፣ ንጽህናዉ የተጠበቀ መጸዳጃቤቶች፣ ወዘተ.ናቸዉ፡፡ እነዚህ ፍላጎቶች ሊሟሉ የሚችሉት በመንግስት በጀት፣ በማህበረሰብ ተሳትፎ፣ በተለያዩ በጎ አድራጊ ግለሰቦች እና ድርጅቶች፣ ወዘተ. ናቸዉ፡፡

### መልመጃ 4.1

**መመሪያ፡-ቀጥሎ ለቀረቡ ጥያቄዎች መልስ ስጡ፡፡**

1. የቤተሰብ አባላትን ዘርዝሩ ፡፡
2. የጤና ጥቅሞችን ግለጹ፡፡
3. የትምህርት ቤታችሁንና የአካባቢዉን ማህበረሰብ የጋራ ፍላጎት አብራሩ፡፡
4. የእረፍት እጦት ምን ሊያስከትል ይችላል?
5. የአካል ብቃት እንቅስቃሴ የሚያስገኘዉን ጥቅሞች ግለጹ፡፡

## 4.2. በትምህርት ቤት የተማሪዎች አቻ ግንኙነት እና ተግባራት



### ቁልፍ ቃላት

- አቻ ግንኙነት
- ክበባት
- ስነስርዓት
- ተግባራት
- ደንብ

### ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቅ አጥጋቢ የመማር ብቃት

**ዉድ ተማሪዎች!ይህንን ይዘት ተምራችሁ ካጠናቀቃችሁ በኋላ፡-**

- በትምህርት ቤት የተማሪዎች አቻ ግንኙነት ታብራራላችሁ፡፡
- በትምህርት ቤት ዉስጥ የተለያዩ ተግባራትን ታከናዉናላችሁ፡፡

- የክበባት ጠቀሜታ ትዘረዝራላችሁ፡፡
- በክበባት ዉስጥ ትሳተፋላችሁ፡፡
- የትምህርት ቤት ደንብና ስርዓት ታከብራላችሁ፡፡

## የንዑስ ርዕስ ይዘቶች

- በትምህርት ቤት የተማሪዎች አቻ ግንኙነት
- በትምህርት ቤት የተማሪዎች ተግባራት

## 4.2.1. በትምህርት ቤት የተማሪዎች አቻ ግንኙነት

### የተግባር ክንዋኔ 4.7: የቡድን ዉይይት

**ዓላማ**፡- አቻ ግንኙነትን ማብራራት

**መመሪያ**፡- ቀጥሎ ባለዉ ጥያቄ ላይ በቡድን ተወያይታችሁ መልስ ስጡ፡፡

**ጥያቄዎች**፡-

1. አቻ ግንኙነት ማለት ምን ማለት ነዉ?
2. አቻ ግንኙነት ለተማሪዎች ምን ጠቀሜታ አለዉ?

በትምህርት ቤት የአቻ ግንኙነት ማለት በእድሜ እና በትምህርት ደረጃቸዉ ከሞላ ጎደል እኩል የሆኑ ተማሪዎች የሚፈጥሩት የእርስ በርስ ግንኙነት ማለት ነዉ፡፡ ተማሪዎች በሚፈጥሩት የአቻ ግንኙት እርስ በርሳቸዉ በመደጋገፍ ፣ አብሮ በማጥናት፣ አብሮ በመጫወት እዉቀታቸዉንና ማህበራዊ ክህሎታቸዉን ያሳድጋሉ፡፡ ተማሪዎች ከአቻ ግንኙነት ባሻገር በትምህርት ቤት ዉስጥ በተለያዩ ክበባት ለምሳሌ የፀረ ኤድስ ፣ የስፖርት፣ የአካባቢ እንክብካቤ፣ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ፣ የትራፊክ ደህንነት ክበብ፣ ወዘተ. ዉስጥ በአባልነት ይሳተፋሉ፡፡

## 4.2.2.በትምህርት ቤት የተማሪዎች ተግባራት

### የተግባር ክንዋኔ 4.8: የቡድን ዉይይት

**ዓላማ**:- ክበባትን መዘርዘር::

- የክበብ ተሳትፎ ጠቀሜታን መግለጽ::

**መመሪያ**:- ቀጥሎ ባሉት ጥያቄዎች ላይ በቡድን ተወያይታችሁ መልስ አቅርቡ::

**ጥያቄዎች**:-

1. በትምህርት ቤታችሁ ውስጥ የሚገኙትን ክበባት ዘርዝሩ::
2. በክበባት ውስጥ መሳተፍ ለምን ይጠቅማል?
3. የየትኛው ክበብ አባል ናችሁ? የክበቡስ ዓላማ ምንድን ነው?
4. በትምህርት ቤት ክበባትን እንዴት ማቋቋም እንደሚቻል ተወያዩ::

የጎበዝ ተማሪ አንዱ መገለጫው በትምህርት ቤት ውስጥ በሚገኙ ክበባት መሳተፍ ነው::ክበባት የትምህርት ቤቱን እና የአካባቢውን ማህበረሰብ ችግሮች መፍቻ ስለሆኑ ተማሪዎች በንቃት ተሳትፎ ማድረግ አለባቸው:: በክበባት ተሳትፎ ማድረግ ተማሪዎች ከመደበኛው የክፍል ውስጥ ትምህርት በተጨማሪ በህብረተሰብ ውስጥ ስለሚኖራቸው ጉልህ ድርሻ ግንዛቤ እንዲይዙ ይረዳቸዋል::

## 4.2.3.የትምህርት ቤት ደንብ እና ስነ-ስርዓት

### የተግባር ክንዋኔ 4.9: የቡድን ዉይይት

**ዓላማ**:- የትምህርት ቤት ደንቦች እና ህጎችን መዘርዘር::

- የትምህርት ቤት ደንቦች እና ህጎችን አስፈላጊነት መግለጽ::

**መመሪያ**:- ቀጥሎ ባሉት ጥያቄዎች ላይ በቡድን ተወያይታችሁ መልስ አቅርቡ::


**ጥያቄዎች**:-

1. የትምህርት ቤት ደንቦች እና ህጎችን ዘርዝሩ?
2. በትምህርት ቤት ደንብ እና ሕግ ለምን አስፈለገ?

የትምህርት ቤት ደንብ እና ስነ-ስርዓት ማለት ሁሉም ተማሪዎች ጠንቅቀዉ ማወቅ የሚጠበቅባቸዉ እና በትምህርት ቤት ቆይታቸዉ የሚያከብሩት ሕግ ነዉ፡፡ እነርሱም የትምህርት ቤት ሰዓት ማክበር ፣የመማሪያ ቁሳቁሶችን በተገቢ መያዝና መጠቀም፣ የሰንደቅ ዓላማ ስነስርዓት ማክበር፣ ወዘተ. ናቸዉ፡፡



ስዕል4/3 የትምህርት ቤት ደንብ እና ስርዓት በክፍል ዉስጥ



ስዕል 4/4 ተማሪዎች የሰንደቅዓላማ ስነ-ስርዓት ሲያከብሩ

መልመጃ 4.2

**መመሪያ:-** ቀጥሎ ለቀረቡት ጥያቄዎች መልስ ስጥ/ጭ::

1. የአካባቢ እንክብካቤ ክበብ ተግባሩ ምንድን ነዉ?
2. በክፍል ዉስጥ ተማሪዎች ማክበር ያለባቸዉ ደንብና ስነ-ስርዓት ምንድን ናቸዉ::

## 4.3. የግል እና የአካባቢ ንጽህና አጠባበቅ

### 4.3.1.የግል ንጽህና አጠባበቅ



**ቁልፍ ቃል**

- የግል ንህና

**ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቅ አጥጋቢ የመማር ብቃት**

**ዉድ ተማሪዎች!ይህንን ይዘት ተምራችሁ ካጠናቀቃችሁ በኋላ:-**

- የግል ንጽህና መጠበቂያ መንገዶችን ትለያላችሁ::
- የግል ንጽህናችሁን ትጠብቃላችሁ::

**የግል ንጽህና አጠባበቅ**

**የተግባር ክንዋኔ 4.10: የግል ሥራ**

**ዓላማ** :- የግል ንጽህናን መጠበቅ ምን ጥቅሞች እንዳሉት መዘርዘር::
- የግል ንጽህና መጠበቂያ መንገዶችን ማብራራት::

**መመሪያ:-** ቀጥሎ የቀረቡትን ጥያቄዎች አንብባችሁ መልስ ስጡ::

**ጥያቄዎች:-**

1. የግል ንጽህና መጠበቅ ማለት ምን ማለት ነዉ?
2. ተማሪዎች! የግል ንጽህናችሁን የምትጠብቁት እንዴት ነዉ?

የግል ንጽህና ማለት አንድ ሰዉ ለሰዉነቱ እና ለሚለብሰዉ ልብስ የሚያደርገዉ ጥንቃቄ ማለት ነዉ፡፡በርካታ የግል ንጽህና መጠበቂያ መንገዶች ሲኖሩ እነሱም ሰዉነትን መታጠብ ፣ ጥርስን መቦረሽ ወይም መፋቅ፣ልብሶችን አጥቦ መልበስ ፣ መጸዳጃ ቤት መጠቀም፣ ቆሻሻን በየቦታው አለመጣል፣ የእንስሳትና የሰዎችን መኖሪያ መለየት ወዘተ.ናቸዉ፡፡



ስዕል 4/5 ልዩ ልዩ የግል ንጽህና መጠበቂያ መንገዶች

## 4.3.2.የአካባቢ ንጽህና አጠባበቅ

**ቁልፍ ቃል**

◆የአካባቢ ንጽህና

**ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቅ አጥጋቢ የመማር ብቃት**

ዉድ ተማሪዎች!ይህንን ይዘት ተምራችሁ ካጠናቀቃችሁ በኋላ፡-

♣ የአካባቢ ንጽህና አስፈላጊነትን ትገልጻላችሁ፡፡

## የአካባቢ ንጽህና አጠባበቅ

### የተግባር ክንዋኔ 4.11: የጥንድ ውይይት

**ዓላማ**:- ስለ አካባቢ ንጽህና ምንነት ማብራራት፡፡

- የአካባቢ ንጽህና ጉድለት የሚያስከትላቸዉን ችግሮች መግለጽ፡፡

**መመሪያ**:- ቀጥሎ ባሉት ጥያቄዎች ላይ በጥንድ ተወያይታችሁ መልስ አቅርቡ፡፡

**ጥያቄዎች**:-

1. የአካባቢ ንጽህና ማለት ምን ማለት ነዉ?
2. የአካባቢ ንጽህና ጉድለት ምን ያስከትላል?

የአካባቢ ንጽህና ማለት አካባቢን ከቆሻሻ እና ከጀርሞች ነጻ ማድረግ ማለት ነዉ፡፡ የአካባቢ ንጽህናን መጠበቅ የሚቻለዉ መንገዶችን በማጽዳት፣ የመጠጥ ዉሃ ንጽህና በመጠበቅ፣ ከቤት የሚወጡ ቆሻሻዎችን በአግባቡ በማስወገድ፣ ወዘተ. ነዉ፡፡



ስዕል 4/6 አካባቢን የማጽዳት ተግባር በከፊል

## 4.3.3.የትምህርት ቤት ንጽህና አጠባበቅ

**የተግባር ክንዋኔ 4.12: የጥንድ ዉይይት**

**ዓላማ**፡- ስለ ትምህርት ቤት ንጽህና ምንነት ማብራራት፡፡

- የትምህርት ቤት ንጽህና አጠባበቅ ዘዴዎችን መዘርዘር፡፡

**መመሪያ**፡- ቀጥሎ ባሉት ጥያቄዎች ላይ በጥንድ ተወያይታችሁ መልስ አቅርቡ፡፡

**ጥያቄ**፡-

1. የትምህርት ቤት ንጽህና አጠባበቅ ዘዴዎችን ዘርዝሩ፡፡

የትምህርት ቤት ንፅህና እንደ ግል ቤታችን ንጹህ አድርገን ብንጠብቅ የጤና ችግሮችን በተሟላ ሁኔታ ለመከላከል እንችላለን፡፡

**የትምህርት ቤት ንጽህና አጠባበቅ ዘዴዎች**፡-

- የመማሪያ ክፍል በንጽህና መያዝ፣
- ደረቅ ቆሻሻዎችን ሰብስቦ ተቆፍሮ በተዘጋጀ ጉድጓድ ውስጥ መጣልና ማቃጠል፣
- የዝንቦች መራቢያ የሚሆኑ እርጥበት ያላቸው ቆሻሻዎችን ማስወገድ፣
- በየሜዳው መጸዳዳትን አስወግዶ ሽንት ቤትን አዘጋጅቶ በመጠቀም የሰዎች አይነምድር ላይ ነፍሳት እንዲይራቡበት ማድረግ፣
- ቆሻሻ ወረቀቶችን በተዘጋጀዉ የቆሻሻ ማጠራቀሚያ (ቅርጫት) ዉስጥ ብቻ መጣል፣
- ዉሃ ፍሳሽ መሄጃ (ቦይ) ማበጀት ወዘተ. ናቸዉ፡፡



ስዕል 4/7 ተማሪዎች የትምህርት ቤት ጽዳት ዘመቻ ተሳትፎ በከፊል

## መልመጃ 4.3

**መመሪያ አንድ፡ ከሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች ዉስጥ ትክክል የሆነዉን "እዉነት" ትክክል ያልሆነዉን "ሐሰት" በማለት መልስ/ሽ፡፡**

1. ንጽህናዉን የሚጠብቅ ተማሪ ለበሽታ አይጋለጥም፡፡
2. የመጠጥ ዉሃ ንጽህና መጠበቅ አያስፈልግም፡፡
3. ከምግብ በፊት እጃችንን በዉሃና በሳሙና መታጠብ አለብን፡፡
4. መፀዳጃ ቤት ዉስጥ መፀዳዳት ለበሽታ ያጋልጣል፡፡
5. ከመፀዳጃ ቤት መልስ እጆቻችንን በሚገባ መታጠብ አለብን፡፡

**መመሪያ ሁለት፡-ቀጥሎ ለቀረቡት ጥያቄዎች ትክክለኛዉን መልስ የያዘ ሆሄ ምረጥ/ጭ፡፡**

1. የግል ንጽህና አጠባበቅ ያልሆነዉ የቱ ነዉ?

ሀ. ጥርስ መቦረሽ　　　ሐ. ጥፍር መቁረጥ

ለ. ያልታጠበ ልብስ መልበስ　　　መ. ሰዉነት መታጠብ

2. የአካባቢ ንጽህና መጠበቂያ መንገድ የሆነው የቱ ነው?

ሀ. ቆሻሻ ማቃጠል | ሐ. ጥፍር መቁረጥ

ለ. ፀጉር መታጠብ | መ. ገላ መታጠብ

## ማጠቃለያ

- የቤተሰብ አባላት ማለት በአንድ ቤት ውስጥ የሚኖሩ ሰዎች ናቸው ፡፡ እነሱም እናት፣አባት ወንድም፣ እህት እና ሌሎችን ያጠቃልላል፡፡
- የሰው ልጅ ሶስት መሠረታዊ ፍላጎቶች አሉት እነሱም ምግብ፣ ልብስና መጠለያ ናቸው፡፡
- ጤና ማለት አካላዊ፣አዕምሮአዊ እና ማህበራዊ ደህንነት ማለት ነው፡፡ የተሟላ ጤንነት ያለው ሰው ጠንካራ፣ንቁ፣ተግባቢ፣ደስ ተኛና በስራ ው ውጤታማ ነው፡፡ ጤነኛ ለመሆን የተመጣጠነ ምግብ መብላት፣ በቂ እረፍት መውሰድ እና አካላዊ እንቅስ ቃሴ ማድረግ ይኖርብናል፡፡
- የግል እና የአካባቢ ንጽህና መጠበቅ ለተለያዩ በሽታዎች የመጋ ለጥ እድል ይቀንሳል፡፡
- የትምህርት ቤት ማህበረሰብ የሚባሉት በትምህርት ቤት ውስጥ የሚያገለግሉ እና የሚገለገሉ ሲሆኑ የትምህርት ቤት አካባቢ ማህበረሰብ የምንላቸው በትምህርት ቤት ዙሪያ የሚኖሩ ማህበ ረሰብ ናቸው፡፡

**የትምህርት ቤት ማህበረሰብ እና የአካባቢ ማህበረሰብ ንጹህ የትምህርት/ቤት አካባቢ፣ምቹ የመማሪያ ክፍሎች፣ጤናማ ተግባቦት፣ቀልጣፋ አገልግሎት፣ የተሟላ የቁሳቁስ አቅርቦት፣የንጹህ ውሃ አቅርቦት፣ የስፖርት ማዘውተሪያ ቦታዎች፣ ቤተ መጽሀፍ፣ንጽህናው የተጠበቀ መጸዳጃ ቤቶች፣ ወዘተ. ይፈልጋሉ፡፡ ትምህርት ቤታችን የተለያዩ ደንቦች እና ስነ ስርዓት መመሪያዎች አሉት፡፡ ደንቦቹንም ሆነ ስነ-ስርዓቶቹን ማክበር ተገቢ ነው፡፡**

**የትምህርት ቤት ደንብና ስነ/ስርዓት የሚባሉት፡-**

ሀ. የትምህርት ቤት ሰዓት ማክበር
ለ.ጥያቄ እጅ አንስቶ መጠየቅ
ሐ.የትምህርት ቤቱን ማሕበረሰብ ማክበር
መ. የደንብ ልብስ መልበስ
ሠ. በክበባት ንቁ ተሳትፎ ማድረግ፣
ረ. የመማሪያ ቁሳቁሶችን በተገቢ መንገድ መያዝና መጠቀም
ሰ. የሰንደቅ ዓላማ ስነስርዓት ማክበር
ሸ. የክፍል እና የቤት ሥራዎች ን መሥራት፣ ወዘተ...ናቸዉ፡፡

## የምዕራፉ ማጠቃለያ ጥያቄዎች

**መመሪያ አንድ፡ ከሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች ዉስጥ ትክክል የሆነዉን "እዉነት" ትክክል ያልሆነዉን "ሐሰት" በማለት መልስ/ሽ፡፡**

1. የአካል ብቃት እንቅስቃሴ ለጤንነት አስፈላጊ ነዉ፡፡
2. የትምህርት ቤቱን ስርዓት እና ደንብ ማክበር ጠቃሚ ነዉ፡፡
3. ንጽህናዉ ባልተጠበቀ አካባቢ ጀርሞች አይኖሩም፡፡

**መመሪያ ሁለት፡- ለሚከተሉት ጥያቄዎች ተስማሚ የሆነዉን መልስ ምረጥ/ጭ፡፡**

1. በአንድ ቤት ዉስጥ አብሮ የሚኖሩ ሰዎች ምን ይባላሉ?
   ሀ. ጎረቤት ሐ. ማህበረሰብ
   ለ. ቤተሰብ መ. ግለሰብ
2. ከሚከተሉት ዉስጥ የቤተሰብ አባል ያልሆነዉ የቱ ነዉ?
   ሀ. ወንድም ሐ. ጓደኛ
   ለ. እህት መ. አባት

3. ከትምህርት ቤት ማህበረሰብ ዉስጥ መማር የማን ቀዳሚ ተግባር ነዉ?

ሀ. ወላጅ ሐ. ተማሪ

ለ. ጥበቃ አባል መ. ርዕሰ መምህር

4. የቤተሰብ አባላት መሠረታዊ ፍላጎት ያልሆነዉ የቱ ነዉ?

ሀ. መጠለያ ሐ. ዝነኛ መሆን

ለ. ምግብ መ. ልብስ

5. በቂ እረፍት ማድረግ ምን ጥቅም አለዉ?

ሀ. ድካም ሐ. ንቁ መሆን

ለ. የስራ ፍላጎት ማነስ መ. ብስጭት

6. ከሚከተሉት ዉስጥ የትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ ያልሆነዉ የቱ ነዉ?

ሀ. መምህራን ሐ. የአካባቢ ማህበረሰብ

ለ. ተማሪዎች መ. ጥበቃ

**መመሪያ ሦስት፡-ለሚከተሉት ጥያቄዎች አጭር መልስ ስጥ/ሽ፡፡**

1. የትምህርት ቤት ማህበረሰብና የአካባቢ ማህበረሰብ ፍላጎት ግለጹ
2. በትምህርት ቤት የተማሪዎች አቻ ግንኙነት ማለት ምን ማለት ነዉ?
3. ጤና ምንድን ነዉ?

# ምዕራፍ አምስት

# የተለየ ትኩረት የሚፈልጉ ቁልፍ ጉዳዮች

## ከምዕራፉ የሚጠበቁ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች

ተማሪዎች የዚህን ምዕራፍ ይዘቶች ተምራችሁ ካጠናቀቃችሁ በኋላ:-

- የትራፊክ ደንቦችን ታብራራላችሁ ።
- የትራፊክ ደንቦች አተገባበር ህይወትን እና ንብረትን ከአደጋ እንዴት እንደምጠብቅ ታደንቃላችሁ።
- እራሳቸዉን በደም ንኪኪ ከሚተላለፉ በሽታዎች ለምሳሌ ከኤች አይ ቪ እንዴት እንደሚትከላከሉ ግንዛቤ ታሳድጋላችሁ።

## በምዕራፉ የተካተቱ ይዘቶች

5.1 የመንገድ ትራፊክ ደህንነት

5.2 ጥሩ የጤና አጠባበቅ ልማድ

## መግቢያ

ዉድ ተማሪዎች! በአንደኛ ክፍል የአካባቢ ሳይንስ ትምህርት መንገድ አጠቃቀም፣ ጥሩ የጤና አጠባበቅ ልማድ ተምራችኋል። በዚህ ምዕራፍ ደግሞ ስለ መንገድ ደህንነት ፣ ትራፊክ ሕጎች እና ጥሩ የጤና አጠባበቅ ልማድ ትማራላችሁ።

## 5.1. የመንገድ ትራፊክ ደህንነት



**ቁልፍ ቃላት**

- ትራፊክ ደህንነት
- የትራፊክ አደጋ
- ትራፊክ ሕጎች

### ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቅ አጥጋቢ የመማር ብቃት

ዉድ ተማሪዎች!ይህንን ይዘት ተምራችሁ ካጠናቀቃችሁ በኋላ፡-

- ስለ መንገድ ትራፊክ ደህንነት ትገልጻላችሁ፡፡
- የመንገድ ትራፊክ ሕጎችን ትዘረዝራላችሁ፡፡
- የመንገድ ትራፊክ ሕጎችን ታከብራላችሁ፡፡
- የመንገድ ትራፊክ አደጋ መንስኤዎችን ትናገራላችሁ፡፡
- ትራፊክ አደጋን ለመቀነስ የሚረዱ መንገዶችን ትዘረዝራላችሁ
- ከመንገድ ትራፊክ አደጋ ራሳችሁን ትጠብቃላችሁ፡፡

### የንዑስ ርዕስ ይዘቶች

- የመንገድ ትራፊክ ደህንነት
- የመንገድ ትራፊክ ደህንነት ሕጎች

### 5.1.1.የመንገድ ትራፊክ ደህንነት

**የተግባር ክንዋኔ 5.1: የግል ሥራ**

**ዓላማ** ፡- የመንገድ ትራፊክ ደህንነት መግለጽ

**መመሪያ**፡- ቀጥሎ ለቀረበዉ ጥያቄ መልስ ስጡ፡፡

**ጥያቄ**፡-

1. የመንገድ ትራፊክ ደህንነት ማለት ምን ማለት ነዉ?

የመንገድ ትራፊክ ደህንነት ማለት በሰዉ ላይ በተሽከርካሪ ምክንያት የሚደርሰዉን አደጋ (ሞት እና የአካል ጉዳት) ለመቀነስ የሚረዳ ዘዴ እና እርምጃ ነዉ።

## 5.1.2.የመንገድ ትራፊክ ደህንነት ሕጎች

### የተግባር ክንዋኔ 5.2: የቡድን ዉይይት

**ዓላማ** ፡- የመንገድ ትራፊክ ሕጎችን መለየት።

- የትራፊክ አደጋ መንስኤዎችን መዘርዘር።

**መመሪያ**፡- ቀጥሎ ባሉት ጥያቄዎች ላይ በቡድን ተወያይታችሁ ማብራሪያ አቅርቡ።

**ጥያቄዎች**፡-

1. የመንገድ ትራፊክ ሕጎች የሚባሉት የትኞቹ ናቸዉ?
2. የትራፊክ አደጋ መንስኤዎች ምንድን ናቸዉ?
3. የመኪና መንገድ እንዴት ታቋርጣላችሁ?

የመንገድ ትራፊክ ሕጎች ማለት የመንገድ ትራፊክ ደህንነትን ለማረጋገጥ የሚያስችሉ እና በሁሉም ሰዉ መታወቅ፣ መከበር እና መፈጸም ያለባቸዉ ተግባራት ናቸዉ።



ስዕል 5/1 መንገድ ከማ፝ረጥ በፊት ግራ ቀኝ ማየት





ስዕል 5/2 አስፓልት ባለበት በዜብራ ምልክት ማቋረጥ



ስዕል5/3 በእግር ጉዞ ጊዜ የእግረኛ መስመር መጠቀም



ስዕል5/4 በመኪና መንገድ ላይ ኳስ መጫወት የሚያስከትለዉ አደጋ በከፊል

**መልመጃ 5.1**

**መመሪያ :-ቀጥሎ ለቀረቡ ጥያቄዎች መልስ ስጡ፡፡**

1. የመንገድ ትራፊክ ደህንነት እነማንን ይመለከታል?
2. የመንገድ ትራፊክ ደህንነት ለምን ይጠቅማል?

## 5.2. ጥሩ የጤና አጠባበቅ ልማድ



**ቁልፍ ቃላት**

◆ጥሩ ጤና አጠባበቅ ◆ልማድ

### ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቁ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች

**ዉድ ተማሪዎች!ይህንን ይዘት ተምራችሁ ካጠናቀቃችሁ በኋላ:-**

- እራሳችሁን በደም ንኪኪ ከሚተላለፉ በሽታዎች ለምሳሌ ከኤች አይ ቪ እንዴት እንደሚትከላከሉ ግንዛቤ ታሳድጋላችሁ፡፡
- ከደም ንኪኪ ራሳችሁን ትጠብቃላችሁ፡፡

### ጥሩ የጤና አጠባበቅ ልማድ

**የተግባር ክንዋኔ 5.3: የቡድን ዉይይት**

**ዓላማ**:- በደም ንኪኪ የሚተላለፉ በሽታዎችን መናገር፡፡

- የደም ንኪኪ መከላከያ መንገዶችን መዘርዘር ፡፡

**መመሪያ**:- ቀጥሎ ባሉት ጥያቄዎች ላይ በቡድን ተወያይታችሁ መልስ አቅርቡ፡፡

**ጥያቄዎች**:-

1. በደም ንኪኪ የሚተላለፉ በሽታዎችን ጥቀሱ?
2. የደም ንኪኪ ልከሰት የሚችልባቸዉ መንገዶች ጥቀሱ
3. ራሳችሁን ከደም ንኪኪ መከላከያ መንገዶችን ዘርዝሩ፡፡

ጥሩ የጤና አጠባበቅ ልማድ ማለት እራስንና ሌሎች ሰዎችን ከተላላፍ በሽታዎች መጠበቅ ማለት ነዉ፡፡ በሌላ አባባል በማንኛዉም ማህበራዊ ግንኙነቶቻችን (በሃዘንና በደስታ ጊዜ) እራሳችንና ሌሎችንም በደም፣በትንፋሽ እና በማንኛዉም ሰዉነት ፈሳሾች ልተላለፉ ከሚችሉ በሽታዎች መከላከል ማለት ነዉ፡፡ በተለይ የደም ንኪኪ ለተለያዩ አደገኛ እና መድሃኒት ለሌላቸዉ በሽታዎች ለምሳሌ ለኤች አይ ቪ፣ለጉበት በሽታ የመሳሰሉት ያጋልጣል፡፡ ስለዚህ ከማንኛዉም ከደም ንኪኪ ራሳችንን መጠበቅ ይኖርብናል፡፡

**የደም ንኪኪ ልከሰት የሚችልባቸዉ መንገዶች:-**

- ስለታማ መሳሪያዎችን(ምላጭ፣ መቀስ፣መርፌ ወዘተ.)በጋራ መጠቀም
- የጥርስ መፋቂያ(ብሩሽ) በጋራ መጠቀም
- የሰዉን ቁስል በእጅ መንካት
- በአደጋ ጊዜ ( የሚደማ ሰዉን) ያለ ጓንት መንካት
- የተጣሉ ማንኛዉንም ቆሻሻ ነገሮችን (ሶፍት፣ጥጥ፣ጓንት ወዘተ.) መንካት፡፡

**የደም ንኪኪ መከላከያ መንገዶች**

- ስለታማ መሳሪያዎችን(ምላጭ፣ መቀስ፣መርፌ፣ጥፍር መቁረጫ ወዘተ.) በጋራ አለመጠቀም
- የጥርስ መፋቂያ (ብሩሽ) በጋራ አለመጠቀም
- የሰዉን ቁስል በእጅ አለመንካት
- በአደጋ ጊዜ ( የሚደማ ሰዉን) ያለ ጓንት አለመንካት
- በወሊድ ጊዜ ንኪኪ አለማድረግ
- ማንኛዉንም ቆሻሻ ነገሮችን አለመንካት ወዘተ. ናቸዉ፡፡

## መልመጃ 5.2

*መመሪያ :-ቀጥሎ ለቀረቡ ጥያቄዎች መልስ ስጥ/ጭ፡፡*

1. ጥሩ የጤና አጠባበቅ ልማድ ማለት ምን ማለት ነዉ?

2. በደም ንኪኪ የሚተላለፉ በሽታዎችን ጥቀስ/ሽ፡፡
3. በደም ንኪኪ የሚተላለፉ በሽታዎችን መከላከያ መንገዶችን ዘርዝር/ሪ;;

## ማጠቃለያ

- የመንገድ ትራፊክ ደህንነት ማለት በሰዉ ላይ የሚደርሰዉን አደጋ ለመቀነስ የሚረዳ ዘዴ እና እርምጃ ነዉ፡፡
- በደም የተበከሉ ቁሳቁሶችን በጋራ መጠቀም ለበሽታ መዛመት መን ስኤዎች ስለሆኑ መጠንቀቅ ያስፈልጋል፡፡
- ጥሩ የጤና አጠባበቅ ልማድ ማለት እራስንና ሌሎች ሰዎችን ከተላላፍ በሽታዎች መጠበቅ ማለት ነዉ፡፡

**የደም ንኪኪ ልከሰት የሚችልባቸዉ መንገዶች፡-**

- ስለታማ መሳሪያዎችን (ምላጭ፣ መቀስ፣መርፌ፣ወዘተ.) በጋራ መጠቀም
- የጥርስ ብሩሽ በጋራ መጠቀም
- የሰዉን ቁስል በእጅ መንካት
- በአደጋ ጊዜ ( የሚደማ ሰዉን) ያለ ጓንት መንካት
- የተጣሉ ማንኛዉንም ቆሻሻ ነገሮችን (ሶፍት፣ጥጥ፣ጓንት ወዘተ.) መንካት ወዘተ. ናቸዉ፡፡

**የደም ንኪኪ መከላከያ መንገዶች**

- ስለታማ መሳሪያዎችን(ምላጭ፣ መቀስ፣መርፌ፣ጥፍር መቁረጫ ወዘተ.) በጋራ አለመጠቀም
- የጥርስ ብሩሽ በጋራ አለመጠቀም
- የሰዉን ቁስል በእጅ አለመንካት
- በአደጋ ጊዜ ( የሚደማ ሰዉን) ያለ ጓንት አለመንካት
- በወሊድ ጊዜ ንኪኪ አለማድረግ
- ማንኛዉንም ቆሻሻ ነገሮችን አለመንካት ወዘተ. ናቸዉ፡፡

## የምዕራፉ ማጠቃለያ ጥያቄዎች

**መመሪያ አንድ፡-ከሚከተሉትን ዓረፍተ ነገሮች ዉስጥ ትክክል የሆነዉን “እዉነት” ትክክል ያልሆነዉን “ሐሰት” በማለት መልሱ፡፡**

1. ኩርባ ባለበት ቦታ የመኪና መንገድ ማቋረጥ የማይመከረዉ የሚመጣ ተሽከርካሪ ስለማይታይ ነዉ፡፡
2. እግረኛ አስፓልት ማቋረጥ የሚችለዉ የዜብራ ምልክት ባለበት ነዉ፡፡
3. እግረኛ የዜብራ ምልክት ባለበት ግራ ቀኝ ሳያይ አስፓልት ማቋረጥ ይችላል፡፡
4. ግራ ቀኝ ሳያዩ መንገድ ማቋረጥ የትራፊክ አደጋ ያመጣል፡፡
5. ኤች አይ ቪ /ኤድስ በማንኛዉም የደም ንክኪ ይተላለፋል፡፡

**መመሪያ ሁለት፡- ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛዉን መልስ የያዘዉን ሆሄ ምረጥ/ጭ፡፡**

1. እግረኛ መጓዝ የሚገባዉ በየትኛዉ መስመር ነዉ ?
   - ሀ. በቀኝ መስመር
   - ለ. በግራ መስመር
   - ሐ. በመኪና መንገድ መሀል
   - መ. መልሱ አልተሰጠም፡፡
2. ከሚከተሉት ዉስጥ ለትራፊክ አደጋ አጋላጭ የቱ ነዉ?
   - ሀ. በእግር ጉዞ ላይ እያሉ ለመንገድ ትኩረት አለመስጠት
   - ለ. በመኪና መንገድ ላይ ኳስ መጫወት
   - ሐ. የእግረኛ መንገድ ትቶ በመኪና መንገድ መጓዝ
   - መ. ሁሉም ለአደጋ አጋላጭ ናቸዉ
3. ከሚከተሉት ዉስጥ የደም ንኪኪ መከላከያ መንገድ ያልሆነዉ የቱ ነዉ?
   - ሀ. ስለታማ መሳሪያዎችን በጋራ አለመጠቀም
   - ለ. ማንኛዉን የወዳደቁ ነገሮችን አለመንካት
   - ሐ. የሰዉን ቁስል መነካካት
   - መ. የጥርስ ቡሩሽ ወይም መፋቂያ በጋራ አለመጠቀም

*መመሪያ ሦስት፡-ለሚከተሉት ጥያቄዎች አጭር መልስ ስጥ/ጭ፡፡*

1. የመንገድ ትራፊክ ደህንነት ጠቀሜታ ዘርዝር_ሪ፡፡
2. የትራፊክ አደጋ በአካባቢያችሁ በስፋት ይከሰታል?
3. የትራፊክ አደጋዎችን እንዴት መቀነስ ይቻላል?
4. ጥሩ የጤና አጠባበቅ ልማድ እንዴት ማጎልበት ይቻላል?